# በአገልግሎት ቅድሚያ ለምን እንደሚሰጥ ማወቅና ማድረግ

የአገልጋይ ሕይወት የሚለው አሳብ አንድ አገልጋይ እንደ አማኝ፣ እንደ ባለትዳርና ወላጅ እንዲሁም እንደ ቤተክርስቲያን አገልጋይ /ሠራተኛ እንዴት መኖር አለበት? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። የአገልጋይ ሁለንተናዊ ሕይወት ምን ይመስላል? በሀገራችን ሁኔታ አገልጋይ ሕይወቱን እንዴት እየኖረ ይገኛል? ይህ የኑሮ ዘይቤ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ላይ የሚያስከትለው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድነው? አገልጋይ ስኬታማ የወንጌል አገልጋይ ለመሆን ለምን ዓይነት ነገሮች ቅድሚያ መስጠት አለበት? በዚህ ክፍል እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንመልሳለን።

## አገልጋይ እንደ አማኝ

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ አስቀድሞ የሚጠራው ለድነት እንደሆነ የታወቀ ነው። ለአገልግሎት መጠራት ከድነት በኋላ የሚመጣ ነው። የአገልግሎት መሠረቱ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ መታረቅ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ራሱን እንደ አገልጋይ ከማየቱ በፊት ራሱን እንደ አማኝ ማየት አለበት። አንድ አገልጋይ አማኝ መሆኑ ቀረ ማለት ከአገልጋይነቱ ተሻረ ማለት ነው። አንድ ሰው አገልጋይ የሚባለው አማኝ በመሆን እስከኖረበት ጊዜ ነው።

አገልጋይ አማኝ መሆኑን ሲዘነጋ መንፈሳዊ ሕይወቱ እየከሰመ ይሄዳል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነቱ ይላላል። ይህ ደግሞ የሕይወት ባዶነትና ትርጉም ማጣትን ያስከትላል። ከዚያም አገልግሎቱ ይደርቅበታል። በፊት የነበረው ደስታና እርካታ ይጠፋበታል። ይህን የውስጥ ባዶነቱንና በአገልግሎት እርካታ ማጣቱን በመገንዘብ ራሱን ማስተካከል የማይፈልግ ከሆነ አገልገሎቱ አሰልቺ ሥራ ይሆንበታል:: ከዚያም በውስጡ የተፈጠረውን አለመረጋጋት ላለማሳወቅ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሁከት እንዲፈጠር ያደርጋል:: በቤተክርስቲያን ውስጥ ችግር የሚፈጥሩ አገልጋዮች ትክክለኛ አማኝ መሆን የተሳናቸው ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ አገልጋይ የግል ሕይወቱም ተበላሽቶበት ቤተክርስቲያንንም ከማነጽ ይልቅ ማፍረስ እንዳይጀምር ዘወትር ትክክለኛ አማኝ ሆኖ መኖር አለበት፣ ምን ጊዜም አማኝ መሆኑን መርሳት የለበትም።

አገልጋይ እንደ አማኝ መሆንና ማድረግ የሚገባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም ጥቂቶች ለግንዛቤ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

### *እግዚአብሔርን ማወቅ*

አገልጋይ እንደ አማኝ እግዚአብሔርን በግሉ ያወቀ ሰው መሆን አለበት። እግዚአብሔርን ማወቅ በአንድ ጊዜ የሚያልቅ ትምህርት

ባይሆንም የሚያመልከውና የሚያገለግለው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በሚገባ ሊያውቀው ይገባል። እግዚአብሔርን በግሉ የሚያውቅ ከሆነ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእምነቱ መቆም ይችላል። ሌሎች የተከተሉት ሰዎች እንኳ እግዚአብሔርን ትተው ወደ ሌላ አምልኮ ዘወር ቢሉ እርሱ ግን ጌታ ማን እንደሆነ ስለሚያውቅ በእምነቱ ይጸናል (ዮሐ.6፡66-68)።

አማኝ እግዚአብሔርን ማወቅ የሚችለው በማረፍ ነው። እግዚአብሔር *"ዕረፉ! እኔም አምላክ እንደሆንሁ እወቁ"* (መዝ.46:10) በማለት ይናገራል። እግዚአብሔርን በትክክለኛ ማንነቱ ማወቅ የሚቻለው ቆም ብሎ ስለእርሱ በማሰላሰል ነው።

*መጸለይ*

አማኝ ያለጸሎት መኖር አይችልም። ጸሎት አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር መንፈሳዊ ተራክቦ የሚያደርግበት ዓይነተኛ መንገድ ነው። የአማኝ ሕይወት ከጸሎት ከተለየ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነቱ ይቋረጣል። አማኝ ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ጸሎት ማድረግ ይገባዋል። የእግዚአብሔር ቃል ምዕመናንን ሳያቋርጠ እንዲጸልዩ ይመክራል። ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ሳይታክቱ ዘወትር መጸለይ እንዳለባቸው የሚያሳስብ አንድ ምሳሌ ነግሮአቸው ነበር (ሉቃ.18:1-8)። ጳውሎስም ምዕመናን በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር በጸሎት መቅረብ እንዳለባቸው «ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1ተሰ.5:17) በማለት አሳስበአቸዋል። የምዕመናን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

አገልጋይ እንደ አማኝ በጸሎት የሚተጋ መሆን አለበት። ያለጸሎት ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር አይቻልም። ያለ መልካም መንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ የእግዚአብሔርን የልቡን አሳብ ማገልገል አይታሰብም። በአሁኑ ወቅት አገልጋዮች እንደሚገባ እንዳይጸልዩ ያደረጋቸው የአገልግሎት መብዛት ነው። በእርግጥ የአገልጋዮች እጥረት ባለበት ሁኔታ የአገልግሎት ጫና እንደሚበዛ የታወቀ ነው። ሆኖም ለጸሎት ትኩረት መስጠት ለሕይወትና ለአገልግሎት ስኬት ቁልፍ ነው። አገልጋይ ጸሎት ለሕይወቱና ለአገልግሎቱ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት መማር ይችላል። ጌታ ምንም አገልግሎት ቢበዛበት እና እርሱን በጣም የሚፈልጉት ሰዎች ቢኖሩም ለጸሎት ትኩረት ወይም ቅድሚያ ይሰጥ ነበር (ማር.1:32-35፣ 6:46፣ ሉቃ.5:15-16፣ 6:12)።

አገልጋይ ራሱን ካስለመደ አገልግሎቱን በማይነካ ሁኔታም መጸለይ ይችላል። አንድ አገልጋይ ማለዳ በመነሳት በእግዚአብሔር ፊት ቢቀርብ ለቀን አገልግሎቱ የሚበቃውን ኃይል ከጌታ ዘንድ ተቀብሎ ይወጣል። ይህን ለማድረግ ማለዳ ለመነሳትና ለመጸለይ ራስን ማሰልጠን ያስፈልጋል። አገልጋይ የማለዳውን ጸሎት ከቤተሰቡም ጋር መጸለይ ይችላል። የጸሎት ጊዜው የግድ ረጅም መሆን አያስፈልገውም። ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሚያገኘው ወይም ኃይል የሚኖረው ለረጅም ጊዜ ስለጸለይን ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነታችን ልክ ነው። ይህ ማለት ግን ለጥቂት ደቂቃ መጸለይ ብቻ ይበቃል ማለት ሳይሆን ትኩረት መደረግ ያለበት በልምምዱ ላይ እንጂ በጸሎት በምናሳልፈው ጊዜ ላይ መሆን

የለበትም ማለት ነው:: ሁኔታዎች ሲመቹ ለረጅም ጊዜ መጸለይ ካልሆነ ደግሞ ቢያንስ ለዚህ ደቂቃ ያህል ማለዳ ማለዳ በእግዚአብሔር ፊት መቆየት አለብን የሚል ደንብ ቢኖረን መልካም ነው::

አገልጋይ ማለዳ ብቻ ሳይሆን ማታም መጸለይ ይኖርበታል:: አገልግሎቱን ጨርሶ ማታ ወደ ቤቱ ሲገባ ከቤተሰቡ ጋር መጸለይና ቃልን መካፈል እጅግ አስፈላጊ ነው:: ቀን ሌሎችን ሰዎች ሲያገለግል ይውላል፣ ማታ ደግሞ ቤተሰቡን ያገለግላል:: ይህን የቤተሰብ አምልኮ ልንለው እንችላለን:: የቤተሰብ አምልኮ ለጥሩ ቤተሰብ ግንባታና ለአገልግሎት ስኬት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን አገልጋይ ማለዳና ማታ ብቻ መጸለይ አለበት ማለት አይደለም:: ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች ለአንድ አገልጋይና ለቤተሰቡ እንደ ደንብ ሆነው ሁሌ የሚያደርጋቸው ቢሆኑ መልካም መሆኑን ለማሳየት እንጂ አገልጋይ ለሰዓታት ወይም ለቀናት በእግዚአብሔር ፊት ሆኖ መጸለይ ይችላል:: አልፎ አልፎ የሚደረጉ ድርጊቶችን እንደ ሕይወት ዘይቤ መውሰድ አስቸጋሪ ይሆናል::

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሆነ ስለሚታመን ሰዎች በጸሎት ላይ ያለን ሰው አይረብሹም:: ሰው ሲፈልገውም «ጸሎት ላይ ነው» ይባላል:: በሀገራችን ሰዎች በሕይወታቸው ከሌሎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የተወሰነ ወሰን ባይኖራቸውም በጸሎት ግን ወሰናቸውን ይጠብቃሉ:: ከዚህም የተነሳ አንድ ሰው እየጸለየ እያለ ከጸሎት ላይ ማቋረጥ የተለመደ አይደለም:: ስለዚህ ጸሎት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መንፈሳዊ ተግባር እንደሆነ ይታመናል:: ይህ አስተሳሰብ መልካም ነው:: አንድ ሰው እየጸለየ ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ስለሆነ ማንም ሰው ጣልቃ ገብቶ መረበሽ የለበትም:: ስለዚህ አገልጋይም ሲጸልይ ምዕመናን "አንተን ለአገልግሎት እንፈልግሃለን" በማለት እንዳይጸልይ እንቅፋት ሊሆኑበት አይገባቸውም::

አገልጋይ የጸሎት ጊዜ ሳይኖረው ዘወትር ከምዕመን ጋር መገናኘቱ በራሱ ሙሉ አገልግሎት አይደለም:: የአገልጋይ ከምዕመኑ ጋር መሆን ፍሬያማ የሚሆነው አገልጋይ በእግዚአብሔር ፊት ቆይቶ ከእነርሱ ጋር ሲገናኝ ነው:: ጸጋ ያለው አገልግሎት የሚመጣው ከጌታ ጋር ቆይታ ካደረጉ በኋላ ነው:: ይህ ማለት ግን አገልጋይ ከምዕመናን ጋር ከመገናኘት ይልቅ ዝም ብሎ መጸለይ አለበት ማለት አይደለም:: ለሁሉም ነገር የተመደበ ጊዜ ሊኖር ይገባል:: ስለዚህ ምዕመናን የአገልጋዮችን የጸሎት ጊዜ ሊያከብሩና ወሰኑን ሊጠብቁ ይገባቸዋል:: የአገልጋይ መጸለይ ጥቅሙ ለአገልጋዩ ብቻ ሳይሆን ለሚያገለግላቸውም ምዕመናን ጭምር ስለሆነ በሁሉም ዘንድ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል::

### *የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ*

አንድ ሰው በዚህ ዓለም ለመኖር ለሥጋው የሚያስፈልገውን ምግብ ማግኘት የግድ ነው:: እንደዚሁም ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወትም መንፈሳዊ ምግብ መመገብ አስፈላጊ ነው:: ይህም መንፈሳዊ ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል ዕለት ዕለት መመገብ ይኖርበታል:: አንድ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ የሚችለው ተመጣጣኝ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ ማለትም የእግዚአብሔርን ቃል

ሲመገብ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር የሚያጠና አማኝ ቃሉ በአዕምሮው ውስጥ በሙላት ይኖራል በዚህም "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ" (ቆላ.3፡16) የሚለውን ትዕዛዝ በተግባር ይተረጉማል። የእግዚአብሔር ቃል በአማኝ ሕይወት ውስጥ በሙላት ሲኖር አማኙ በሕይወቱ የሚመጣበትን ማንኛውንም ፈተና ለመቋቋም ኃይል ያገኛል፤ ድል የነሳ የክርስትን ሕይወት መኖር ይችላል።

አገልጋይ ልክ እንደ አንድ ምዕመን ቃሉን መመገብ አለበት። አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ለመመገብ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠና ከሆነ መስመሩን ስቷል። አገልጋይ ሌሎችን ምን ላስተምር ብሎ ከማሰቡ በፊት እግዚአብሔር ለሕይወቴ ምን ይለኛል? በማለት ቃሉን ለራሱ ሕይወት ማጥናት አለበት። የአገልጋዩ ሕይወት ከተገነባ በኋላ ለሌሎች የሚሆነውን መልዕክት ከእግዚአብሔር ያገኛል። የእግዚአብሔርን ቃል ለግል መመገብ የሚለው አሳብ ቃሉን ለሌሎች ከማስተማሩ በፊት አገልጋይ ከቃሉ አኳያ የራሱን ሕይወት መመልከትና መመዘን እንዳለበት ያመለክታል። ቃሉ አስቀድሞ በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ ሥራ ሠርቶ ካለፈ ሰሚዎች ይባረኩበታል። አገልጋዩ ከቃሉ አኳያ የት እንዳለ በማሳየት እርምጃውን እንዲከተሉ አቅጣጫ ያሳያቸዋል።

ስለዚህ አገልጋይ ለሌሎች ምግብ የሚያዘጋጅ ብቻ ሳይሆን ለግሉም ምግቡን አዘጋጅቶ የሚበላ ሰው መሆን ይገባዋል። መልካምን ምግብ አዘጋጅቶ በልቶ ያላጣጣመ ሰው እንዴት መልካም ነው ብሎ ለሌሎች መስጠት ይችላል? ስፖንጅ በውስጡ ውኃን የሚያስተላልፈው ለራሱ የሚበቃውን ያህል ውኃ ከመጠጠ በኋላ ነው። አገልጋይም በሕይወቱ ሞልቶ ከተረፈው ቃል ለሌሎች ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። ይህ አገልጋይ በእግዚአብሔር ቃል የተሞላ እና ቃሉን አስቀድሞ በሕይወቱ በተግባር ላይ ያዋለ መሆን እንዳለበት ያመለክታል።

ይህ ማለት ግን አገልጋይ በሕይወቱ ያልደረሰበትን ነገር ማስተማር የለበትም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። አገልጋይ በሕይወቱ መሆንና ማድረግ የሚገባውን ግን ያልደረሰበትን መልካም አሳብ በማስተማር ሰሚዎች ወደዚህ መልካም ዕድገት እንዲመጡ ሊጋብዛቸው ይችላል። እርሱና ምዕመናኑ በዚያ ትምህርት አኳያ አብረው ወደፊት ይራመዳሉ። አንዳንድ ከአገልግሎት ሥነምግባር የጎደለ ሕይወት የሚኖሩ አገልጋዮች ያልሆኑትን ወይም ያልደረሱበትን ነገር እንደሆኑትና እንደደረሱበት አድርገው ይናገራሉ። እንዲህ ዓይነት ድርጊት ግብዝነት ስለሆነ ውሎ አድሮ እየተገለጠ ይመጣል:: አገልጋይ አሁን እዚህ ነን፤ ግን ከዚህ ሁኔታ ወጥተን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ደረጃ እልፍ ማለት አለብን በማለት ማስተማር ይችላል። ራሱም ሆነ የሚያገለግላቸው ምዕመናን ወዳልደረሱበት ሙላት እንዲደርሱ ቃሉን ያማከለ ትምህርትና ልምምድ ማስተማር ኃላፊነቱም ነው::

*በመንፈስ ቅዱስ መሞላት*

የክርስትና ሕይወት ሰው በራሱ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል የሚኖረው ሕይወት ነው። አማኝ ጌታ ኢየሱስን ሲቀበል

የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናል። ይህ ማለት ግን መሙላቱ አያስፈልግም ማለት አይደለም። በሀገራችን በተከሰተው የዝናብ እጥረት ሳቢያ የግድቦች የውኃ መጠን በመቀነሱ የኤሌክትሪክ ፍጆታ በፈረቃ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው። ይህ ማለት ውኃ ጠፋ ማለት ሳይሆን ያለው ውኃ ለሥራው ከሚፈለገው መጠን በታች መሆኑን ያሳያል። በተመሳሳይ መልክ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም። መንፈስ በሕይወቱ በሙላት በመኖር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወትና አገልግሎት እንዲኖር ሊያደርገው ይገባል።

የመንፈስ በሕይወቱ ውስጥ መኖር ብቻ ሳይሆን በሙላት መገኘት አስፈላጊ ስለሆነ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይኖርበታል። ይህ ሲሆን አሸናፊ የሆነ ሕይወት ይኖራል። መንፈስ ቅዱስ በሙላት በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሲኖር የሚያደርጋቸው ተግባሮች ብዙ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ምዕመናንን ያበረታታል፣ ይመራል፣ ያስተምራል፣ ኃጢአት ሲሠሩ በመውቀስ ወደ እግዚአብሔር አሳብ ይመልሳቸዋል፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖርና እግዚአብሔርን እንደ ፈቃዱ ለማገልገል የሚበቃቸውን ኃይል ይሰጣቸዋል። ምዕመናን እግዚአብሔር በሕይወታቸው ስለሠራው መልካም ነገር ላላመኑ ሰዎች መመስከር የሚችሉት መንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ነው። ጌታ ይህን ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ....ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (ሐዋ 1:8) በማለት ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው። የጌታ ምስክሮች ከመሆን በፊት ከጌታ ጋር በሚገባ መተዋወቅና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላት የግድ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ አማኝ ለጌታ ምስክር መሆን አይችልም። የምስክርነት ብቃትን የሚሰጠው በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሞልቶ የሚሠራው መንፈስ ነው።

*ጌታቸው ጌታ ኢየሱስን ያመነው በስደቱ ወቅት ነበር። በዚያን ጊዜ ከጥቂት የትምህርት ቤት ወገኖች ጋር በመሆን አብሮአቸው ይጸልይ ነበር። እነዚያ ወንድሞችና እህቶች በጌታ የቆዩና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ነበሩ። ለጸሎት ሲሰበሰቡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ። ደስ እያላቸው እየዘለሉ ይጸልያሉ። አንዳንድ ጊዜ ጎረቤት እስኪሰማቸው ድረስ ይጮሁ ነበር። ጌታቸው የሚያደርጉት ነገር እንግዳ ስለሆነበት የኅብረቱ መሪ የነበረውን ወንድም ይጠይቃል። ያ ወንድም ስለመንፈስ ቅዱስና ስለሙላቱ ለጌታቸው አስረዳው። ጌታቸውም ልቡን ቢያዘጋጅና እግዚአብሔርን ቢጠይቀው እንደሚሞላው ነገረው።*

*ከዚያም ጌታቸው ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መጸለይ ጀመረ። እግዚአብሔር እንዲሞላው ለብዙ ወራት ከጸለየ በኋላ ምንም ምላሽ አላገኘም። ከዚያም ወንድሞች እንዲጸልዩለት ጠየቃቸው። እነርሱም ጸለዩለት። ግን አልተሞላም። ይህን በተከታታይ ለስድስት ወራት አደረገ። በዚህ ወቅት ጌታቸው አንድ ነገር ማሰብ ጀመረ። "እኔ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ እንደነዚህ ወገኖች በልሳን መናገር ካልቻልኩ ይህ እምነት ሐሰተኛ እምነት ነው። ከተሞላሁ ግን ይህ እምነት ትክክለኛ ስለሆነ በሕይወቴ ዘመን እከተለዋለሁ" በማለት ወሰነ። ምናልባት ሰው የውኃ*

ጥምቀት ሳይወስድ በመንፈስ ቅዱስ ላይሞላ ይችላል ብሎ ስላሰበ ጸሎቱን አላቋረጠም።

አንድ ቀን ከገጠር ትምህርቱን ወደሚማርበት ከተማ ለምዝገባ መጣና አንድ ጌታን የማያውቅ ቤተሰብ ቤት ውስጥ በእንግድነት አደረ። ሰዎቹ ጌታን የማያውቁ ስለሆነ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ተነስቶ መጸለይ ጀመረ። ድንገት ሳያስብ ከዚህ በፊት ተናግሮ በማያወቅ አዲስ ቋንቋ መናገር ጀመረ። ሕይወቱ በታላቅ ደስታ ተሞላ። ዝለል! ዝለል! የሚያሰኘው ትልቅ ሐሴት በውስጡ ሞላው። ከዚያም ድምጹን ሳያሰማ እስከንጋት ድረስ ጸለየ። ጌታቸው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት እውነት እንደሆነ ተረዳ። እስከዛሬም በጌታ ቤት አለ። ከዚያም በላይ እግዚአብሔርን በሙሉ ጊዜው እያገለገለ ይገኛል። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሕይወቱ ትልቅ መንፈሳዊ ልምምድ እንደሆነና ለሕይወቱም ሆነ ለአገልግሎቱ መሰረት እንደሆነ ያምናል።

አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ መሞላቱ በምን ይታወቃል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ታሪክ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማስረጃ ሆኖ የቀረበው በልሳን መናገር ነው። በአዲስ ልሳን መናገር መጀመር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አንዱ መታወቂያ መንገድ ነው። ሌሎችም አስፈላጊ ማወቂያ ምልክቶች አሉ። ለምሳሌ ያህል

- እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ ማመስገን (ሐዋ 2:4፣47፤ 10:46፤ 1ቆሮ.14:2)። መንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ በሆነለትና እና ባልሆነለት ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ከማጉረምረም ይልቅ እግዚአብሔር በሕይወቱ ያደረገውን ጥቂቱን ነገር በመቁጠር ጌታን ያመሰግናል። ከችግር ነጻ እንደሆነ ያውጃል ማለት ሳይሆን የሕይወትን መልካም ገጽታ ለማየት የተከፈተ ልቦና ይኖረዋል። በምስጋና ውስጥ ድል እንደሚገኝ ያምናል። ስለዚህ ጌታን ያመሰግናል። የምስጋና ርዕስ አያልቅበትም።
- ኃጢአትን የሚጸየፍ ሕይወት መኖርና እግዚአብሔር ኃጢአተኝነትን እንደሚጠላ በማወቅ የጽድቅ ሕይወት ለመኖር መመኘትና ራስን ከዓለም እርኩሰት ማራቅ። መንፈስ ቅዱስ ዓ ለምን ስለኃጢአት ይወቅሳል። በመንፈስ የተሞላ ሰውም ስለኃጢአት ማንም ሳይነግረው ይረዳል (ዮሐ.16:8)።
- እግዚአብሔርን የሚያስከብር መልካም ሕይወት ይኖራል። የሕይወቱ ዓላማ ጌታ ኢየሱስን ለማክበር ነው። የራሱን ክብር አይፈልግም (ዮሐ.16:13-14፤ ሐዋ.4:33)።
- በሕይወቱ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ይገለጣሉ። ቤተክርስቲያንን የሚያንጹ ስጦታዎችን ያገኛል፤ በእነዚያም ስጦታዎች የክርስቶስን አካል ይገነባል (1ቆሮ 12:4-10)።
- ከሌሎች በስመ ክርስቲያን ከሚመላለሱ ሰዎች ይልቅ የበለጠ የጸሎት ሕይወት ይኖረዋል። ጸሎትን የሚናፍቅ ሕይወት አለው። ጸሎት አይሰለቸውም። ግን ሥራ ትቶ እቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ሁሌ ይጸልያል ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርን ሁሌ ይናፍቃል፣ ያደርግማል ለማለት ነው (ሐዋ.3:1)።

- ለእግዚአብሔር ቃል የጠለቀ ፍቅር አለው። ከዚህም የተነሳ ቃሉን ለመረዳት ጊዜ ሰጥቶ ያጠናል (ዮሐ.16:13፤ ሐዋ.2:42)።
- እግዚአብሔርን እንደ አፍቃሪ አባት ማየት ይጀምራል (ገላ.4:6)። በጌታ የዳነ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም መንፈሱ በውስጡ ይመሰክርለታል (ሮሜ.8:15)።

በተለይ አገልጋይ ሆኖ የእግዚአብሔርን ሥራ በዚህ ክፋት በሞላበት ዓለም ውስጥ መሥራት ያለእግዚአብሔር መንፈስ ሙላት እጅግ አዳጋች ነው። ለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ ወደ ዓለም ከመሄዳቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንደሚያስፈልጋቸው የነገራቸው (ሉቃ24:49)።

መንፈስ ቅዱስ በኃይል በእነርሱ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልና ድፍረት በማግኘት የእግዚአብሔርን መልዕክት ለሕዝብ አስተላለፉ። በዚህም መልዕክት የብዙዎች ልብ ተነክቶ በጌታ አመኑ፣ ወደ ቤተክርስቲያንም ተጨመሩ (ሐዋ. ምዕ. 2)። የሚገርመው ሙላቱ በአንድ ጊዜ ያበቃ አልነበረም። እነዚሁ ሰዎችና ሌሎችም በሌላ ጊዜም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። በአንድ ጊዜ መንፈሳዊ ልምምድና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብቻ ዕድሜ ልክ ማገልገል አይቻልም። አገልጋይ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን በአስፈላጊው ወቅት ማግኘት አለበት።

ሐዋርያት(በሐዋ.2) ላይ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው የእግዚአብሔርን ሥራ በሚገባ መሥራት ቻሉ። ከዚያም ስደት፡ እየበረታባቸው መጣ። ብዙ መሰናክሎች ከፊታቸው ተደቀኑ። በወቅቱ የነበሩ ሃይማኖት መሪዎች ሐዋርያት ወንጌልን እንዳያሰብኩ ከለከሉአቸው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ በውስጣቸው የሞላው መንፈስ የቀነሰ ይመስላል። ይህን ስለተረዱ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። *"...አሁንም ጌታ ሆይ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፣ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፣ ባሪያዎችህም በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው"* (ሐዋ.4:29-30) በማለት ከጸለዩ በኋላ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በፍጹም ግልጥነት መናገር ቻሉ። ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወት ሲደክም እና አገልግሎት ሲሰለች እንዲሁም የተለያዩ መሰናክሎች ሲበዙ እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲሞላን መጸለይ ይገባናል። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከችግሩ በላይ ያስኬደናል።

*የመንፈስ ፍሬ ማፍራት*

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መልካምና አስፈላጊ ነገር ቢሆንም የመንፈስ ፍሬ ተከትሎ የማይመጣ ከሆነ ሙሉ ያልሆነ ሕይወታችን ሙሉ አይሆንም። አንድ ሰው አማኝ መሆኑ የሚታወቀው በልሳን በመናገሩ ሳይሆን በሕይወቱ የመንፈስ ፍሬ በመታየቱ ነው። በልሳን መናገርንስ ክፉም ሊሰጥ ይችላል። የመንፈስ ፍሬ ግን የማይከረጅ የክርስቲያን መታወቂያ ነው።

የመንፈስ ፍሬ የሚባሉት መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ በሙላት በመኖሩ የሚታዩ የሕይወት ባህርያት ናቸው። እነዚህም (በገላ.5:22-23) ላይ ተጠቅሰዋል። "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።" እነዚህ የመንፈስ ፍሬ ተብለው የተጠቀሱት ባህርያት አንድ ምዕመን ከሌሎች ሰዎች ጋር በመስማማት ይኖር ዘንድ ሊኖረው የሚገባውን አመለካከትና ተግባሮችን የሚያሳዩ ናቸው።

እንግዲህ አገልጋይ እንደ አንድ ምዕመን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በተከታታይ የማይለማመዳቸው ከሆነ ለአገልግሎት ሲወጣ የነበረው የውስጥ ኃይሉ ተሟጦ ያልቃል፣ መንፈሳዊ ቅንዓቱ ይለዝባል፣ በሕይወቱ ባዶነት ይሰፍናል፣ የተለያዩ ፈተናዎችን መቋቋም ያቅተዋል፣ ከዚያም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይገባል። ይህ እንዳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጸሎትና ቃሉን በማጥናት መትጋት እንደዚሁም ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍ መኖር ይገባዋል።

ስለዚህ አገልጋይ ከማንኛውም አገልግሎት ይልቅ ለራሱ መንፈሳዊ ሕይወት ትኩረትና ቅድሚያ መስጠት ይጠበቅበታል። አማኝ እነዚህን ነገሮች የሚያደርጋው ለሌሎች ብሎ ሳይሆን ለግል ሕይወቱ በማሰብ እንደሆነ ሁሉ አገልጋይም አስቀድሞ የሚያደርጋቸው ነገሮች ለግል ሕይወቱ ጥቅም እንደሆኑ መገንዘብ ይኖርበታል። አገልግሎት ሙያ ሳይሆን ሕይወት ስለሆነ አስቀድሞ አገልጋዩን ሠርቶ ለሌሎች ሊተላለፍ ይገባል። የአገልግሎት የኃይል ምንጩ አገልጋይ እንደ አማኝ የሚኖረው መንፈሳዊ ሕይወት ነው። የአገልጋይ መንፈሳዊ ሕይወት ጠንካራ ሲሆን አገልግሎቱ ፍሬያማ ይሆናል።

## አገልጋይ እንደ ባለትዳር/ወላጅ/

ከላይ እንደተጠቀሰው አንድ አገልጋይ ከአገልግሎት በፊት ለግል መንፈሳዊ ሕይወቱ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ እንዳለበት አይተናል። ወደ ቤተሰብ ጉዳይ ስንመጣ ደግሞ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ለቤተሰብ ነው ወይስ ለአገልግሎት? የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ከሆነ የቤተሰብ ሕይወት ከአገልግሎት በፊት መምጣት አለበት።

አገልጋይ ከአገልግሎት በፊት ቤተሰቡን ማስቀደም አስፈላጊ መሆኑን ቢያውቅም ይህን ሲያደርግ አለመታየቱ ራሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም አገልግሎቱን ለአደጋ በማጋለጥ ላይ ይገኛል። አገልጋይ እንደ ባለትዳርና ወላጅ ለቤተሰቡ ሊሰጥ የሚገባውን ትኩረት የማያደርገው ለምንድነው? ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልሶች ሊሰጡ ቢችሉም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. *እግዚአብሔርን ማገልገል ለቤተሰብ ትኩረት ከመስጠት እንደሚበልጥ ማሰብ፦* አንዳንድ አገልጋዮች እግዚአብሔርን እንዳገለገሉ የሚያስቡት ከቤተሰባቸው ውጭ ሲያገለግሉ ነው። ለዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መሠረት የሆነውን አንድ ሰው ቤተሰቡን ካልተወ በስተቀር እግዚአብሔርን መከተል አይችልም የሚለውን ቃል በተሳሳተ መንገድ መተርጎም ነው። ጌታ ኢየሱስ እርሱን መከተል የሚሹ ሰዎች ሁሉ ከማንም በላይ እርሱን መውደድ እንዳለባቸው ሲያስተምር የተናገራቸውን

አሳቦች ከአውዱ ውጭ የሆነ ትርጉም በመስጠት በአገልግሎት ስም ቤተሰቦቻቸውን የሚሠዉ አገልጋዮች አሉ:: ጌታ ኢየሱስ «ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱንም፣ ልጆቹንም፣ ወንዶሞቹንም፣ እኅቶቹንም፣ የራሱንም ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ሳይጠላ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም» (ሉቃ.14:26) ማለቱ አገልጋይ ቤተሰቡን በመጥላት ለአገልግሎት እንዲወጣ የሚጋብዝ ጥሪ አይደለም:: ታዲያ እንዲህ ካልሆነ ጌታ ስለምን ለማስተማር ነው ይህን ቃል የተናገረው? .......

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን አገልግሎት የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው። ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቁ ሊሆን የሚችለው ቤተሰቡን እንደሚገባ የሚያገለግልና የሚመራ ሰው ነው። ለኤጲስ ቆጶስነት ከተጠቀሱት መስፈርቶች አንዱ "ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር" (1ጢሞ3:7) መሆን እንደሆነ ይናገርና "ሰው የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃል?" በማለት የአገልግሎት ብቃት መፈተኛ ቦታ ቤተሰብ መሆኑን ያስረዳል።

2. *በአገልግሎት ምክንያት ከቤተሰብ ችግር መሸሽ*፦ አገልጋይ ቤተሰቡ ውስጥ(በተለይም ከትዳር ጓደኛው ጋር) ስምምነት ከሌለው ችግሩን ላለመጋፈጥ የሚሸሽበት አንዱ መንገድ በአገልግሎት ስም ከቤት ውጭ ብዙውን ጊዜ ማሳለፍ ነው።

*ታመነ አገልግሎት ከጀመረ ሁለት አስርት ዓመታት አስቆጥሯል። ከሚስቱ ሁለት ልጆችን ወልዷል። ሚስቱ በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥራ ጥሩ ደመወዝ ታገኛለች። ታመነና ሚስቱ ብዙ ጊዜ ስምምነት የላቸውም። ነገር ግን በመካከላቸው ያለውን ችግር የሚያውቁ በጣም የሚቀርቡአቸው ጓደኞቻቸው ብቻ ናቸው። ሁለቱ ችግሮቻቸውን መናገር አይፈልጉም። ከዚህ ችግራቸው ለመሸሽ ታመነ ሁሉጊዜ ለመስክ አገልግሎት ይወጣል። ብዙውን ጊዜ ከክልል ወደ ክልል እየተዘዋወረ ያገለግላል። አንድ ሳምንት አንድ ቦታ ከሄደ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ክልል ይሄዳል። እቤት የሚያድረው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ሲመጣ ብቻ ነው። ልጆቹ የአባታቸውን ፍቅር አያውቁም፣ የምታሳድጋቸው እናታቸው ናት። ታመነ አገልግሎትን ስለወደደ ሳይሆን አገልግሎትን ከትዳር ችግር የማምለጫ መንገድ ስላደረገው ከቦታ ቦታ ያለማቋረጥ ይሄራል።*

እንደ ታመነ ዓይነት ሰው በቤተክርስቲያን ሥር ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ ቤተክርስቲያን ስለቤተሰቡ ሁኔታ ልትጠይቀው ይገባታል። በራሱ ፈቃደኝነት ችግሩን ለመፍታት እርምጃ መውሰድ ባይፈልግም ቤተክርስቲያን ቤተሰብ እየፈረሰ አገልግሎቱን መቀበል የለባትም። አገልጋዩ የሚያስተምረው ትምህርት አስቀድሞ በቤተሰብ ሕይወቱ ውስጥ በተግባር ሊተረጎም ይገባል።

ከቤተክርስቲያን ውጭ በተለያዩ ሚኒስትሪዎች የሚያገለግሉ አገልጋዮችም ቢሆኑ አገልግሎታቸውን የሚቀበሉ ወገኖች የአገልጋዮቹን የቤተሰብ ሁኔታ መጠየቅ ይገባቸዋል:: በማንኛውም ደረጃና ሁኔታ እግዚአብሔርን አገለግላለሁ የሚል አገልጋይ ስለቤተሰቡ ሲጠየቅ እውነተኛና ግልጽ የሆነ ምላሽ ሊሰጥ ይገባዋል:: አንድ አገልጋይ «እኔ ቤተሰቤን ለእግዚአብሔር ሰውቻለሁ» «እግዚአብሔር ለቤተሰቤ እንደሚያስብላቸው

አምናለሁ» «የእኔ ቤተሰብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው» ማለት ከጀመረ ስለቤተሰብ ባለው አመለካከት ወይም በቤተሰቡ ውስጥ ችግር መኖሩን ያመለክታል። ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ችግር መንፈሳዊ ልብስ እያለበሰው ለማለፍ መሞከር ለጊዜው ለሚያዎችን ከማታለል ያለፈ ፍሬ ስለማይኖረው የራስን ስህተት ተቀብሎ ለተገቢው ነገር ቅድሚያ መስጠት ያዋጣል። በቤተሰብ ሕይወት ግንባታ ያልተሳካለት አገልጋይ ቤተክርስቲያንን ለማነጽ ብቃት አይኖረውም።

3. *ከቤተሰብ ኃላፊነት መሸሽ*፡ የቤተሰብ ኃላፊ ሆኖ ለቤተሰብ የሚያስፈልገውን ሁሉ ማድረግ በራሱ ትልቅ አገልግሎት ሆኖ ሳለ አንዳንድ አገልጋዮች ልጆችን ማሳደግና መንከባከብን ለሚስቶቻቸው በመተው በአገልግሎት ስም ከቦታ ቦታ ይዞራሉ። የቤተሰብን ኃላፊነት ከባድ ነው። ባሎች በአገልግሎት ስም ሲዞሩ የቤተሰብ ኃላፊነት የምትሸከመው ሚስት ናት።

አገልጋይ እንደባለትዳር /ወላጅ/ የቤተሰቡን ቁሳዊ፣ ማህበራዊ፣ መንፈሳዊና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሊያሟላ ይገባዋል። አገልጋይ የሚያገኘው ቀለብ የቤተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት እንዳለበት ቢታመንበትም የብዙ አገልጋዮች ቤተሰብ የሚበሉት፣ የሚለብሱት ነገር አጥተው መቸገራቸው "አገልጋይ ከመሆንስ ለማኝ መሆን ይሻላል" ያሰኛል።

አገልጋይ ቀለቡን በተመለከተ ለቤተሰቡ የማይበቃ ከሆነ ለቤተክርስቲያን መሪዎች መናገር አለበት። ቀለቡን የማሻሻል ሥራ ግን እርሱ ማድረግ የማይችለው ነገር ነው። ሆኖም ከመናገር መቆጠብ የለበትም። ቤተሰቡ እየተራበና እየታረዘ እያየ በይሉኝታ ተይዞ ዝም ማለት አይገባውም። ይህ መንፈሳዊነት አይደለም።

አገልጋይ ተጠርቶ በሚሠማራበት ጊዜ ስለቀለቡ ከቤተክርስቲያን ጋር መነጋገር አለበት። ከቤተክርስቲያን እንደሚሰጠው ተስፋ የተገባለት ቀለብ ለቤተሰቡ እንደሚበቃው ከትዳር ጓደኛው ጋር መወያየት ይኖርበታል። በቤተሰቡ ላይ በራሱ ብቻ መፍረድ አይገባውም። አገልጋይ ስንት ይከፈለኛል? ብሎ መጠየቅ ያልተለመደ ነገር ቢሆንም በኋላ ከማጉረምረም አስቀድሞ መጠየቅ የተሻለ ነው። በአንዳንድ ቦታዎች ስለሚሰጠው ቀለብ የሚጠይቅ አገልጋይ ለቀለብ ብቻ ብሎ እንደሚያገለግል ተደርጎ እንደሚቆጠር የታወቀ ነው። ሆኖም «ስንት ይከፈለኛል?» ብሎ መጠየቅ ግልጽነት እንጂ ስግብግብነት አይደለም። ይህ ቀለብ የማይበቃው ከሆነ በዚህ ቀለብስ ቤተሰቤን ማስተዳደር አልችልም ብሎ በሚበቃው ቀለብ ለአገልግሎት ሊያስማሩ የሚችሉትን ቤተክርስቲያናት መፈለግ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ ደግሞ ለራእዩ ብሎ ከቤተሰቡ ጋር በመስማማት በመጠነኛ ቀለብ ወይም ያለምንም ክፍያ ሌላ የገንዘብ ማግኛ መንገድ ፈልጎ ማገልገል ይችላል።

ቤተክርስቲያን ለአንድ አገልጋይ የሚበቃውን ቀለብ መስጠት የማትችል ከሆነች አገልጋዩ ቤተሰቡን በረሃብ አለንጋ ማስገረፍ የለበትም። አገልጋዩ ከቤተሰቡ እና ከቤተክርስቲያን ጋር በመነጋገር ከሚከተሉት አንዱን ማድረግ ይችላል።

- በትርፍ ጊዜው ሌላ ሥራ በመሥራት ቤተሰቡን የሚደግፍበት ገንዘብ ማግኘት
- የትዳር ጓደኛው ለቤተሰብ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት የምትችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- በሌላ ቤተክርስቲያን በትርፍ ጊዜው ወይም ግማሽ ጊዜ በማገልገል ቀለብ ከሁለት ቤተክርስቲያናት እንዲከፈለው ማድረግ እና ሌሎች የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ይችላል።

አገልጋይ ለቤተሰቡ በተለይም ለትዳር ጓደኛው ተገቢወን ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ትዳራቸው ሊጎዳ ይችላል። መልካም ጋብቻን መመሥረት በቂ ጊዜ መስጠትን ይጠይቃል። አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው በቂ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ እንዴት ፍቅር ያለበት የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል? ግንኙነት በተዓምር የሚፈጠር ሳይሆን ጥረትን የሚጠይቅ ነው። አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው በቂ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ግንኙነታቸው ዕለት ተዕለት እየላላ ይሄዳል። አፍሴላዊ ፍቺ ባያደርጉም ሁለቱ ተለያይተው ይኖራሉ። አገልጋዩ አምሽቶ ወደ ቤት ይገባል። ሚስት ሥራ ካላት ጧት አገልጋዩ ከእንቅልፉ ከመነሳቱ በፊት ወደሥራ ትሄዳለች። ሁለቱም ለምሳ ወደቤት አይገቡም። በዚህ ሁኔታ መቼ የጋራ ጊዜ ይኖራቸዋል? አንዳንዴ ደግሞ ለአገልግሎት እሩቅ ሥፍራ ይሄድና ሰንባብቶ ይመለሳል። የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ ስለአገልግሎት ብትጠየቅ ምን ትናገር ይሆን!

የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ በአገልግሎት ምክንያት ትኩረት እንዲነፈጋት ባትፈልግም እግዚአብሔርን ከመፍራት የተነሳ አገልጋዩን "እባክህን ለእኔም ጊዜ ስጠኝ" ማለትን ትፈራለች። ከዚህም የተነሳ በአምልኮ ቦታ፣ በማህበራዊ ክንውኖች (ለቅሶ፣ ግብዣ...) የአገልጋይ ሚስት ብቻዋን ትታያለች። ሌሎች ባለትዳሮች ጥንድ ሆነው ሲሄዱ እርሷ ለብቻዋ ወይም ከሌሎች ጋር ተዳብላ ትሄዳለች። ባል እያላት ያለባል ሆነች።

ይህን ሁኔታ የተመለከቱ ያላገቡ ሴቶች አገልጋይ ለማግባት ሲጠይቃቸው "ብቻዬን ልቀመጥ ነው እንዴ!" "ያለጊዜ ባልቴት መሆን አልሻም"ይላሉ። ይህ አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው ትኩረት እንደማይሰጥ የታወቀ መሆኑን ያመለክታል። እውነትም የአገልጋይ ሚስት የባልዋን ፍቅር ሳትቀምስ ብቻዋን ልጆቿን የምታሳድግ የልጆች እናት ናት።

ከላይ ለተጠቀሱት ነባራዊ ችግሮች መፍትሔ ሊመጣ የሚችለው አገልጋይ ቤተሰብ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ሲያውቅና ለተግባራዊነቱም እርምጃ ሲወስድ ነው። እንደ መንፈሳዊ መሪ ይህ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ አማኝ የሚያስፈልገው ነገር መሆኑን ማስተማር ይጠበቅበታል። ከዚያም የራሱን ቤተሰብ በሚገባ በመንከባከብ የሚያገለግላቸው አማኞች የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉት ማድረግ አለበት።

አገልጋይ የቤተሰቡንም የስሜት ዋስትና ማሟላት ይጠበቅበታል። የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ በአገልግሎት ዙሪያ የተሰማትን ስሜት የመናገር ወይም የመግለጽ ነጻነት ሊሰጣት ይገባል። ባልዋ አገልጋይ ስለሆነ ዘወትር እንደ አገልጋይ ሚስት ደስ ደስ የምትሰኝ ሴት እንድትሆን

የሚጠበቅ ከሆነ አንድ ቀን የታመቀ ስሜትዋ ሲፈነዳ ወደ መጥፎ ባህርያት ሊመራት ይችላል።

አገልጋይ የትዳር ጓደኛው ስለአገልግሎቱም ሆነ ስለቤተክርስቲያን ያላትን አሳብና ስሜት መግለጽ እንድትችል መፍቀድ እንጂ ማፈን አይገባውም። ሚስቱም ስትገልጽለት ትኩረት ሰጥቶ ሊያዳምጣትና ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። "የአገልጋይ ሚስት እንዲህ ወይም እንዲያ መናገር ወይም መሆን የለባትም" ማለት ችግርን ከመፍታት ይልቅ ሌላ ችግር ይጨምራል።

በመንፈሳዊ ነገር የአገልጋይ ቤተሰብ ጌታን ትቶ ወደ ኋላ ይመለሳሉ ባይባልም በጌታ ያላቸው ደስታና መንፈሳዊ መነቃቃት ወይም ቅንዓት ሊዳከም ወይም ሊጠፋ ይችላል። አገልጋይ ለሌሎች ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት እንክብካቤ የሚያደርገውን ያህል ለቤተሰቡ አያደርግም። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ አገልግሎትን እንደ ሥራ ይቆጥረውና መንፈሳዊ ተግባሮችን ለምሳሌ ጸሎት፣ ቃል ማካፈል፣ አምልኮ መምራት፣ መዘመር... ሲያከናውን ውሎ ወደ ቤት ሲመጣ ሲሠራ ከነበረው ሥራ ማረፍ ይፈልጋል። ውጭ ሲያደርጋቸው የዋላቸውን ነገሮች እንደገና ቤቱ ማድረግ ይሰለቸዋል። ከዚህም የተነሳ የቤተሰቡን መንፈሳዊ ሕይወት ቸል ይላል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያካፍለው ሲጋጩ ብቻ ይሆናል። ባልና ሚስት መልካም ግንኙነት ከሌላቸው፣ የትዳር ጓደኛው ሌሎች የሚያውቁትን ደካማ ጎኑን ስለምታውቅ እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ለእርሷ ሲያስተምራት ለመቀበል ፈቃደኛ አትሆንም። ከዚህም የተነሳ አገልጋይ ለቤተሰቡ ማስተማርን ይተዋል። አንድ ጊዜ አንድ አገልጋይ ቤተሰቦቹን በተለይ የትዳር ጓደኞችውን የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን ከተማረ በኋላ "ባለቤቴ የጌታን ቃል ሳስተምራት ሆን ብዬ የእርስዋን ደካማ ጎን ወይም ችግር አንስቼ የምነግራት እየመሰላት እኔን መስማት አትፈልግም" በማለት ተናገረ። ባልና ሚስት አብሮ ስለሚኖሩ አንዱ የሌላውን ደካማ ጎንና ችግር እንደሚያውቅ የታወቀ ነው። አገልጋይ ቃል ሲያካፍል ሆን ብሎ የሚስቱን ደካማ ጎን የሚጠቅስ ከሆነ መልካም አቀራረብ አይደለም። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል መከታ በማድረግ ሌላውን መውቀስ ወይም መኮነን ነው። አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው እንዲሁም ለቤተሰቡ ቃል ማካፈል ያለበት በቤት ውስጥ ሰላም ሲኖር መሆን አለበት። እንዲህ ከሆነ ሰዎች ቃሉን ከምንም ነገር ጋር ሳያያይዙ በሙሉ ልባቸው መስማትና መቀበል ይችላሉ።

አገልጋይ ከትዳር ጓደኛው ጋር መልካም ግንኙነት ከሌለውና አብረው የእግዚአብሔርን ቃል የማይመገቡ ከሆነ በአገልግሎቱ ስኬታማ አይሆንም። ምክንያቱም አገልጋዩ ዘወትር የሕሊና ወቀሳ ይሰማዋል። በራሱ ቤተሰብ ከሚስቱ ጋር የማይኖረውን ቃል ለሌሎች እንደሚሰብክ ሕሊናው ይወቅሰዋል። እንደዚሁም የበታችነት ስሜት ይሰማዋል። አገልግሎቱ በቤቱ ውስጥ ተቀባይነት እንደሌለው ከሚስቱ ምላሽ አግኝቷል። ከቤተሰብ የጀመረው መናቅ ደግሞ በሌሎችም ሊገጥመው እንደሚችል በማሰብ ተስፋ ይቆርጣል፤ አገልግሎቱም ፍሬ እንደሌለው

አድርጎ እንዲያስብ ያደርገዋል። በመጨረሻም ብቸኝነት ይሰማዋል። በአገልግሎቱ ከእርሱ ጎን በመቆም "አይዞህ በርታ" የሚለው ሰው ያለው አይመስለውም። ምክንያቱም የእርሱ የቅርብ ወዳጅም ከእርሱ ጋር በመሆን አገልግሎቱን እንደማትደግፍ አገልግሎቱን በቤት ውስጥ ባለመቀበል ገልጻለታለች።

ያአገልግሎት ትኩረት የምትፈልገው ሚስት ብቻ ሳትሆን ልጆችም ጭምር ናቸው። አንዳንድ ልጆች ወላጆቻቸው እቤት እንዲሆኑ አይፈልጉም። ወላጆቻቸውን ስለማይወዱአቸው "ምንነው አንድ ቀን እንኳ ከቤት ቢወጡልን" ይላሉ። የብዙ አገልጋዮች ልጆች ደግሞ "መቼ ይሆን አባታችን ጊዜ ኖሮት ከእኛ ጋር የሚጫወተው" እያሉ ያለቅሳሉ። ልጆች ወላጆቻቸውን ሲፈልጉ የወላጆች አለመገኘት ልጆችን ክፉኛ ይጎዳቸዋል። የአገልጋይ ልጆች በአብዛኛው ለእናታቸው የተተዉ ናቸው። ከአባታቸው ጋር የሚገናኙት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው። እናታቸው የውጭ ሥራ የምትሠራ ከሆነች ደግሞ የልጆቹ ዕድል ፈንታ በቤት ሠራተኛ እጅ ማደግ ነው።

አገልጋይ ልጆቹ ራሳቸው የቤተክርስቲያን አካል በመሆናቸው እንደ ልጆቹ ብቻም ሳይሆን እንደ ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባል አገልግሎት ስለሚያስፈልጋቸው ጊዜ በመመደብ ተገቢውን እንክብካቤ ሊሰጣቸው ይገባል። እንዲህ ካልሆነ ልጆቹ ከአባታቸው አገልግሎት የማያገኙት እነርሱ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ ያነሱ በመሆናቸው ይመስላቸዋል።

አንዳንድ የአገልጋይ ልጆች አገልጋይ መሆን መልካም እንዳልሆነ ያስባሉ። እንዲህ እንዲያስቡ ያደረጋቸውም ዋና ምክንያት አገልግሎት አባታቸውን ከእነርሱ በመለየቱ ነው። በተለይ አገልጋዩ ከቤት እሩቅ ወደሆነ ቦታ እየሄደ የሚያገለግልና ለረጅም ጊዜ ከቤተሰብ ተለይቶ የሚቆይ ከሆነ ልጆች አገልግሎት መልካም ነው ብለው ማሰብ አይችሉም። ልጆች «ዛሬ አባባ ለምን ቆየ?» ብለው እናታቸውን ሲጠይቁ እናት «እርሱ እኮ ለአገልግሎት ክፍለ ሀገር ሄዷል» የምትላቸው ከሆነ አገልግሎት አባታቸውን ከእነርሱ እንደለየው ይቆጥራሉ። ስለዚህ አገልጋይ አገልግሎት የሚጀምረው ከቤተሰብ መሆኑን በማወቅ ለቤተሰቡ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል።

አገልጋይ ብቻም ሳይሆን ቤተክርስቲያንም አገልጋይ ለቤተሰቡ ትኩረት እንዲሰጥ የአገልግሎት ፕሮግራሞቹን በማመቻቸትና ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን እንክብካቤ መስጠቱን በመከታተል ልትረዳው ትችላለች። ከዚህም በላይ ባልና ሚስትን አንድ ላይ ለአገልግሎት መጥራትም አማራጭ መፍትሔ ሊሆን ይችላል። በአንዳንድ ቤተእምነት ባልና ሚስት አንድ ላይ እንዲያገለግሉ አይፈቀደም። በአገልግሎት እንዲደጋገፉ፣ አብረው መውጣትና መግባት እንዲችሉ አንዱ ሌላውን መጠራጠር እንዳይችል ባል.ና ሚስት ጥንድ ሆነው ማገልገል መቻላቸው መልካም ሆኖ እያለ ይህ አለመፈቀዱ በጣም ያሳዝናል።

ቤተክርስቲያንም አገልጋይ ቤቱን እያፈረሰ የሌላው ቤት እንዲገነባ ከማድረግ ልትቆጠብ ይገባታል። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለች ከጊዜ በኋላ የአገልጋይ ቤተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት ሲበላሽ ምሳሌነቱ ክፉኛ

ቤተክርስቲያንን እንደሚጎዳ እንዲሁም ባላመኑት ዘንድ መልካም እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርባታል።

## አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ

ቤተክርስቲያን አገልጋይን እግዚአብሔር ጠርቶ ቀብቶ እንዳስነሳው ታምናለች። አገልጋይም በሙሉጊዜው በሙሉ ልቡ የወንጌልን ሥራ እንዲሠራ ይጠበቅበታል። የአገልጋይ ትልቁ ሥራ ሁሉንም መንፈሳዊ አገልግሎት ራሱ መሥራት ሳይሆን ምዕመናን እግዚአብሔር በሰጣቸው ልዩ ልዩ ጸጋ ማገልገል እንዲችሉ ማስተባበርና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ ለሥራ ከፍተኛ የልብ መነሳሳት ያለው ሰው ሊሆን ይገባል:: የልብ መነሳሳቱም መምጣት ያለበት እግዚአብሔር በውስጡ ካስቀመጠው የአገልግሎት ሸክም ነው:: አገልጋይ የሚያገለግለው ጌታ ለዚያ ሥራ ስለጠራው ነው:: የአገልጋይ የልቡ አሳብ በውጫዊ ቀስቃሽ ነገሮች ለምሳሌ በጥሩ ደመወዝ፣ ዝና ወዘተ ነገሮች ብቻ የሚቀሰቀስ መሆን የለበትም:: እንዲህ ከሆነማ ለደመወዝ ከሚሠሩት ሰዎች በምን ይለያል! አገልጋይ የአገልግሎት መነሳሳት የሚያገኘው ውጫዊ ነገሮች ሲመቻቹለት ከሆነ ውስጣዊ የልብ መነሳሳቱ እየሞተበት ይሄዳል:: ከዚያም የጥሪ ነገር ወደኋላ ይባልና የራሱንና የሌሎች ሰዎችን አሳብ ማገልገል ይጀምራል:: አንድ አገልጋይ እግዚአብሔርን ለማገልገል የውስጥ የልብ መነሳሳት የሚኖረው እግዚአብሔር የአገልግሎት ሸክም በውስጡ ሲያስቀምጥ ነው:: ውጫዊ ማበረታቻ በልብ ውስጥ የአገልግሎት ሸክም እንዲወለድ የማድረግ ኃይል የለውም:: ነገር ግን በአግባቡ ከሆነ በውስጥ ያለውን የአገልግሎት ሸክም እንደሚገባ ለማውጣት ይረዳል::

አገልጋይ ለሥራ የልብ መነሳሳት ያለው ብቻም ሳይሆን የሥራ ዲሲፕሊንን የሚያከብር እንዲሆን ይጠበቅበታል:: ከእነዚህም አንዱ የሥራ ሰዓትን ማክበር ነው::ብዙ አገልጋዮች አንድ ሠራተኛ መሥራት ከሚገባው ሰዓት በላይ ሠርተው የትርፍ ሰዓት ክፊያ እንደማይከፈላቸው የታወቀ ነው:: እነዚህ አገልጋዮች አገልግሎት በሰዓት የተገደበ እንደሆነ አያስቡም:: አገልግሎት ካለ ማገልገል ተግባራቸው ነው:: ከዚህም የተነሳ በጣም ይዝላሉ:: አንዳንዶች ደግሞ አንድ ሠራተኛ መሥራት የሚገባውንም ሰዓት አይሠሩም:: በጉብኝት አገልግሎት ስም ከቢሮ ወጥተው ከሆነ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላኛው ቤት ሲዞሩ ይውላሉ:: የሚፈልጉትን ሰው ባያገኙም ካገኙት ሰው ጋር የመጣላቸውን ነገር አውርተው ይመለሳሉ:: እቢሮ ውስጥ ከዋሉ ደግሞ ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላኛው ቢሮ እየሄዱ ያወራሉ፣ የሚሠሩትን ሰዎች ሥራ ያስፈታሉ:: እንዲህም ሆኖ በወሩ መጨረሻ እንደሠሩ ሠራተኞች ላልሠሩበት ሰዓት ደመወዝ ይቀበላሉ:: ይህ ዓይነት ዲስፕሊን የሌለው ሥራ በአገልጋይ ዘንደ እንዳለ መወራት የለበትም::

የጌታ ባሪያ ለአገልግሎቱ ትጉና እግዚአብሔር በከፈተለት የአገልግሎት በር በተሰጠው ጊዜ በተሰጠው መክሊት ይነግዳል:: ሰዎችንም ከጨለማው ሥር ለማውጣት ዘወትር ይተጋል:: አገልጋይ የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ ጌታ ኢየሱስ «ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ትመጣለች» (ዮሐ.9:4) ብሎ የተናገረውን ቢያስብ መልካም ነው::

አገልጋይ እንደ አንድ የቤተክርስቲያን ሠራተኛ ዝርዝር የሥራ ድርሻ ያለው ሰው መሆን አለበት። የሥራ መዘርዝር የሌለው አገልጋይ የሚሠራውን ሥራ አያውቅም። አገልግሎት የሚመስለውን ሁሉንም ዓይነት ሥራዎችን ይሠራል። አንድ ቀን ግን ምን እንደተሠራ እርሱም ሆነ ሌሎች ሲገመግሙት ምንም ነገር እንዳልተሠራ ይታያል። እንግዲህ ተገቢውን ሥራ ለመሥራት የሥራ መዘርዝር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። በሥራ መዘርዝር አስፈላጊነት ላይ ቢታመንም ግን ይህን ለአገልጋይ የሚያዘጋጀው ክፍል ማን ነው? ለአገልጋይ የሥራ መዘርዝር የሚያዘጋጀው አገልጋይ ራሱ ወይም የሚያስተዳድረው ክፍል ሊሆን ይችላል። አገልጋይ እግዚአብሔር በውስጡ ካስቀመጠው ሸክም አንጻር መሥራት የሚፈልጋቸውን ሥራዎች ዝርዝር ለቤተክርስቲያን መሪዎች ያቀርባል። ከዚያም መሪዎቹ ተወያይተውበት ከተቀበሉ አገልጋዩ በዚያ መሠረት ማገልገል ይችላል። ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ መሪዎች ለአገልጋዩ የሥራ መዘርዝር ያወጡለትና ይሰጡታል። አገልጋዩ አንብቦ ከተረዳ በኋላ ስምምነቱን ካሳየ ያ የሥራ መዘርዝሩ ይሆናል ማለት ነው። በሁለቱም መንገዶች አገልጋዩና የሚያሰማራው ክፍል በሥራ መዘርዝሩ ላይ የጋራ መግባባት ሊኖራቸው ይገባል።

አገልጋይ ከቤተክርስቲያን የሚሰጠውን የሥራ ኃላፊነት ትቶ በግሉ የሚያስበውን ነገር ማድረግ አይችልም። ምክንያቱም በዚያች ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግል «የቀጠሩት» መሪዎቹ ናቸው። ስለዚህ የራሱን ትቶ የእነርሱን መቀበል አለበት። ነገር ግን እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠውን ራእይ ቀስ በቀስ በሚያገለግለው አገልግሎት በመሪዎችና በምዕመናን እይታ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ እግዚአብሔር ወደሚመራው አቅጣጫ ሊወስዳቸው ይችላል። ይህን ለማድረግ ግን በትሕትና ማገልገል መጀመር ወሳኝ ነው። የቤተክርስቲያን መሪዎች የአገልጋይን አሳብ የሚቀበሉት አገልጋዩ የእነርሱን አሳብ እያስተናገደ ግን እግዚአብሔር የሰጠውን ራእይ ቀስ በቀስ በፍቅር ማሳየት ከቻለ ነው። ራእይ የሚሰጠው በአንድ ሰው በኩል ቢሆንም ተግባራዊ የሚሆነው ግን ብዙሃኑ ሲቀበሉት ስለሆነ አብሮት ከማካሄድ በትሕትና መንገድ መሄድ የጌታ ፈቃድ ነው።

አገልጋይ እንደ እግዚአብሔር ሰውና አገልጋይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ መሥራት የሚችል ሰው መሆን አለበት። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ ለአንዱ ጌታ ክብር የሚሠሩ ናቸው። ስለዚህ አንዱ ከሌላው ጋር በመስማማት ማገልገል ይጠበቅባቸዋል።

አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ የአገልግሎት ስኬቱን የሚገመግም ሰው ሊሆን ይገባዋል። በአብዛኛው አገልጋይ ጌታን በሚያገለግልበት ጊዜ የዕድሜ ልክ አገልግሎት እንደ ጀመረ ያስባል። ስለዚህ በተለመደው መንገድ ከማገልገል ውጭ ቆም ብሎ አገልግሎትን መገምገም የተለመደ አይደለም። ከዚህም የተነሳ አንዳንድ አገልጋዮች አያገለገሉ ግን ሳያውቁ ከአገልግሎት መስክ ይወጣሉ። እነርሱ ሳያውቁት የሚያገለግሉበት ሁኔታ ከአገልግሎት ሜዳ ውጭ ያስወጣቸዋል። አገልግሎታቸው ምን ያህል ፍሬ እንዳለው፣ ምዕመኑ ስለአገልግሎታቸው ምን እንደሚል፣ የምዕመኑን መንፈሳዊ ፍላጎት እያረኩ ስለመሆናቸው ምንም አሳብ የላቸውም። እነርሱ ለምዕመኑ ያስፈልጋል ብለው ያሰቡትን መልካም በሚመስላቸው መልክ ይሰጣሉ። መልዕክታቸውና አቀራረባቸው ላሉበት አውድ ተስማሚ መሆኑን አይመለከቱም። አገልግሎታቸውን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ስለማይገመግሙ የአገልግሎታቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው

አያውቁም:: ይህን ቢያደርጉ ኖሮ ደካማ ጎናቸውን በማወቅ ዕለት ዕለት ራሳቸውንና አገልግሎታቸውን ማሻሻል ይችሉ ነበር::

ተጠርቶ በሚያገለግልበት መስክ አገልግሎቱን በየጊዜው መገምገም የአንድ አገልጋይ የሕይወት ደንብ ሊሆን ይገባል:: አንዳንዶች ግምገማ ሥጋዊ እንደሆነ ቢያስቡም አገልግሎትን መገምገም መንፈሳዊ ስለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ይደግፈናል:: እግዚአብሔር ራሱ ፍጥረትን ከፈጠረ በኋላ በተከታታይ ግምገማ በማድረግ አስተያየት ሲሰጥ እንደነበር ከቃሉ እናነባለን (ዘፍ.1:4፣31፣ 6:5-8):: ስለአገልግሎቱ ግምገማ የማያደርግ አገልጋይ የሚያደርገውን የማያውቅ፣ አቅጣጫ የጠፋበት፣ መቼ ከአገልግሎቱ እንደሚሰናበት ማወቅ የማይፈልግ፣ ጌታን እንዴት ደስ ማሰኘት እንዳለበት በትጋት የማይፈልግ ሰው ነው:: ይህ ደግሞ ከአንድ አገልጋይ የሚጠበቅ ባሕርይ አይደለም:: ስለዚህ አገልጋይ በግሉ አገልግሎቱ ምን እንደሚመስል መገምገምና ራሱን ማሻሻል አለበት::

እንግዲህ አገልጋይ እንደ ምዕመን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለተሰጠው ለድነቱ/ለመንፈሳዊ ሕይወቱ/ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትና ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረው ይገባል:: ድነትን መጠበቅ ከአገልግሎት እንደሚበልጥ በተግባር የሚያሳይ አማኝ መሆን ይኖርበታል:: ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሰዎችን የሚያስገባው አገልግሎታቸው ሳይሆን ድነታቸውን መጠበቅና መንከባከብ መቻላቸው ነው:: አገልጋይ እንደ ትዳር ጓደኛና ወላጅም ለቤተሰቡ ሕይወትና ኑሮ የሚጠነቀቅ ሊሆን ይገባዋል:: ለቤተክርስቲያን አገልጋይነት ብቁ ለመሆን ለራሱ ቤተሰብ ሁለንተናዊ እንክብካቤ ማድረጉ ለአገልግሎቱ ስኬት ቁልፉ ነው:: እንዲህ ሲሆን የቤተሰቡም ሕይወት በመልካም ምሳሌነቱ ስለወንጌልና ስለክርስቲያናዊ ኑሮ ምስክር ይሆናል:: ከዚህም በላይ ቤተሰብ ለአገልጋዩ አገልግሎት ድጋፍ ሰጪ አካል ይሆናል:: በመጨረሻም አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ የልብ መነሳሳት ያለው፣ የሥራ ዲሲፕሊንን የሚያከብር፣ ከሌሎች አገልጋዮችና የቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር በመግባባትና በፍቅር አብሮ የሚሠራ እንዲሁም በተሰጠው የሥራ ድርሻ የአገልግሎት ስኬቱን የሚገመግምና ከዛሬ ነገ ራሱን የሚያሻሽል መሆን ይጠበቅበታል::

---

**ጥያቄዎች**

1. እንደ አንድ አማኝ አለኝ የምትለው የሕይወት ልምምድና ጥራት ምንድነው?
2. አገልጋይ እንዴት አገልግሎቱንና የቤተሰብ ሕይወቱን በሚዛናዊ ሁኔታ መያዝ ይችላል?
3. አንድ አገልጋይ ቤተሰቡ እንዲያገለግል ፈቃደኛ ካልሆነ ምን ማድረግ ይኖርበታል ትላለህ? ለምን?
4. አንድ አገልጋይ ማገልገል ያለበትን ሰዓት እንደ ሌሎች ሥራዎች መወሰን ይቻላል? ለምን?
5. አገልጋይ የሚችለውን ሁሉ ጥረት አድርጎ ስኬት ባያገኝ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? ጥረ ካለ ስኬት የግድ መኖር አለበትን? አሳብህን የሚደግፍ ምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አለህ?

# 12
## የአገልጋይ መልካም ባህርያትን መኖር

ለአንድ አገልጋይ መልካም ባህርይ ኖሮት መልካም የጌታ አገልጋይ መሆን እጅግ ከባድ መሆኑ የታወቀ ነው። መልካም የተባሉትን ባህርያት ማግኘት የአገልጋዩና የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። አገልጋይ እግዚአብሔር ከእርሱ የሚጠብቀው መልካም ባህርይ እንዲኖረው አስፈላጊ የሆነውን ጸጋ ይሰጣል። ሆኖም አገልጋዩ ጸጋውን ተቀብሎ እንደሚገባ ሊኖርበትና ራሱንም በጸጋው ሊያሳድግ ይገባዋል። አገልጋይ እግዚአብሔርን ሲያገለግል ሊኖሩት የሚገባው መልካም ባህርያት አሉ። አገልጋይ የላከውን እግዚአብሔርን ባህርይ መልበስ ይጠበቅበታል። አገልጋይ በአገልግሎቱ፣ ፍሬያማ እንዲሆን መልካም ባህርያት ወሳኝ ናቸው። እነዚህም ምን እንደሆኑ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1 **እግዚአብሔርን መምሰል** (1ጢ.ሞ.4፡7)

እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔርን መምሰል ማለት በመልክ የእርሱን "ቅርጽ" መያዝ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መስጠት፣ ከፍቅር የተነሳ እርሱን በመፍራት ማክበር ነው። እግዚአብሔርን መምሰል እርሱን ከልብ በማክበር የተነሳ እርሱን ደስ የሚያሰኝ መልካምና በቅድስና የተሞላ ሕይወት መኖር ነው። እግዚአብሔርን የሚመስል ሰው እርሱን ይወዳል፣ ያከብራል እንዲሁም ይፈራል። በሌላ አነገገር እግዚአብሔርን የማይዳፈረው ግን የሚገባውን አምላካዊ ክብር የሚሰጥ ሰው ነው።

እግዚአብሔርን መምሰል የውስጥ የልብ ምላሽ ብቻ ሳይሆን በአኗኗር ዘይቤም የሚገለጽ ነው። እግዚአብሔርን እየመሰለ የሚኖር ሰው በአኗኗር ዘይቤው እግዚአብሔርን ማዕከላዊ ያደረገ ሕይወት ይኖራል። እግዚአብሔርን በልቡ በማንገስ በአሳብና በተግባር የእርሱን ባህርይ ይገልጻል።

እግዚአብሔርን መምሰል ቁጭ ብሎ ስለመልካም መንፈሳዊ ሕይወት በማሰብ የሚመጣ ክስተት ሳይሆን ራስን ማስለመድን ይጠይቃል። ይህ ልምምድ ደግሞ ከሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴ ጋር ይመሳሰላል። በተለያዩ ዘመናት ብዙ ሰዎች የአካል እንቅስቃሴዎች በተከታታይነት ማድረግ ለአካል ጤንነት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ። ሐኪሞችም የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ ለጤንነት ጥሩ እንደሆነ ከመግለጽም ባሻገር እንደ "መድኃኒትም" ያዛሉ። ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ማለዳ ማለዳ ወይም ምሽት አካባቢ የአካል እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይታያሉ። ይህ በአካባቢያችንም እየተለመደ መጥቷል።

በተመሳሳይ መልኩ አገልጋይ ለጤናማ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሱን ማስለመድ ይገባዋል። እግዚአብሔርን መምሰል ራስን በሥርዓት መምራትን ይጠይቃል። እርሱን መምሰል መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ይከናወናል።

እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚረዱ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ምንድናቸው? ሐዋርያው ጳውሎስ ዝርዝራቸውን አልተናገረም። ሆኖም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ሊያደርጋቸው የሚችሉ መልካምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ልምምዶች ለምሳሌ ቃሉን ዘወትር ማጥናት፣ በተከታታይነት መጾምና መጸለይ፣ ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር መልካም ኅብረት ማድረግ፣ እግዚአብሔርን ማምለክ እና የመሳሰሉት ተግባሮች ይጠቀሳሉ።

በአሉታዊ ጎኑ ደግሞ እግዚአብሔርን ለመምሰል ከማይረዱ ከንቱ አሳቦችና ልምምዶች መራቅ የግድ ነው። "ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶችን ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ" (1ጢሞ.4:7)። አገልጋይ እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር ከእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ትምህርት ማስተናገድ የለበትም። ለጆሮ የሚጥም ወይም ሰዎች በተለምዶ እውነት እንደሆነ የሚተርኩት ፈጠራ ወደ እግዚአብሔር አሳብ አያስጠጋም። ስለዚህ አገልጋይ ከእነዚህ ፈጠራ አሳቦች መራቅ አለበት። በሰዎች ግምት መልካም እንደሆኑና ኑሮን የሚያቃኑ የሚመስሉ አሳቦች ጌታን እየመሰሉ እርሱን ከማገልገል ጋር ሲነጻጸሩ ዘላቂ ውጤት የላቸውም።

እግዚአብሔርን ለመምሰል መትጋትና እርሱን መምሰል ጥቅም አለው። የአካል እንቅስቃሴ ዘወትር ማድረግ ለአካል ጤንነት ጠቃሚ ነው። ከዚህም ሲያልፍ ጥሩ ስፖርተኛ በመሆን ውድድር አሸንፎ ታዋቂ መሆን ወይም ገንዘብ ማግኘትን ያመጣል። እግዚአብሔርን ለመምሰል መትጋት ደግሞ እጥፍ ጥቅም አለው። ጥቅሙ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም የሚታይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ "ለነገር ሁሉ ይጠቅማል" በማለት ይናገራል። ይህ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ መጸለይ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል በተከታታይ ማጥናት እንዴት ለነገር ሁሉ ሊጠቅም ይችላል?

*ታሪኩ ተማሪ በነበረበት ጊዜ ችሎታ ቢኖረውም በሥርዓት ትምህርቱን አያጠናም ነበር። ሲያጠናም አሳቡ ሳይገባው እንዲሁ መሸምደድን እንጂ የአሳቡን ብልት እየወጣ መገምገምና ማሰላሰል አያውቅም ነበር። ጌታን ከተቀበለ እና መጸለይ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ከጀመረ በኋላ ግን የሚማረውን ትምህርት በሚገባ ማሰላሰልና አሳቦችን ብልት ብልታቸውን እየወጣ መመርመር ጀመረ። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ "ዓሣን መብላት በብልሃት" እንደሚባል ስለሆነ አዕምሮው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመረዳት በሚጠቀመው ዘዴ ትምህርቱን ማጥናት ሲጀምር ከዚያ በፊት ተረድቶ የማያውቀውን እውነት መገንዘብ ጀመረ። ታሪኩ ጌታን ከተቀበለ በኋላ የበለጠ ጎበዝ ተማሪ መሆን ቻለ። ለታሪኩ ጌታን ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናቱ ለትምህርቱም አስተዋጽኦ አድርጎለታል።*

እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ ለሁለንተናዊ ሕይወት ይጠቅማል። አገልጋዮች እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያደርጉት መንፈሳዊ ተግባሮች ለሥጋዊ እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይጠቅማቸዋል። መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ

በሚመራበት ጊዜ ኑሮአቸውም እንደ እግዚአብሔር አሳብ ይሆንላቸዋል። ይህ ሲሆን ደግሞ በመብዛትም ሆኖ በመትደል ውስጥ ለእግዚአብሔር የሚመች ሰላም ያለው ሕይወት ይኖራሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መስሎ መኖር ለሚመጣው ዓለምም ትርፍ አለው።

2. **ምሳሌ መሆን** (1ጢሞ 4:12)

አገልጋዮች መሆን ከሚገባቸው ዋነኛ ነገር አንዱ ለሚያገለግሏቸው ሰዎች ምሳሌ መሆን ነው። ምሳሌ መሆን ማለት ሌሎች ሰዎች አይተው መከተል የሚገባቸው ዓይነት ሞዴል መሆን ነው። አገልጋዮች ለተከታዮቻቸው ምሳሌ የሚሆኑት በተለያየ የሕይወት መስክ ነው። ለምሳሌ ያህል በፍቅር፣ በታማኝነት፣ በንጽሕና እግዚአብሔርን በመምሰልና በመጽናት ምሳሌ መሆን ይገባቸዋል።

አገልጋይ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች የሚያሳይ ሞዴል ሊሆን ይገባል። የእግዚአብሔር ፍቅር ምን እንደሚመስል ሰዎች ስለእግዚአብሔር ባህርይ ከሚያስተምረው ሰው ሕይወት ውስጥ ማየት ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የገለጠው ፍቅር ሰዎች ገና ኃጢአተኞች ሳሉ የወደደ (ሮሜ5:8)፣ በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ (ዮሐ3:16) እና ለሰዎች መልካም እንዲሆን እስከሞት ድረስ መስዋዕትነት የከፈለ (ዮሐ.15:13) ፍቅር ነው።

ሰዎች አገልጋይ ለሰዎች ያለውን ፍቅር በማየት "ለካስ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዲህ ይወዳል" ማለት የሚያስችል ሰው እንዲሆን ይጠበቅበታል። ሰዎችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚቀበለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር የማሳያው መንገድ የአገልጋይ ሕይወት ነው። አገልጋይ ይህን ፍቅር የሚያሳየው ሰዎች ምንም ዓይነት ክፉ ነገር ሲናገሩት ወይም ሲያደርጉበት እንዲሁም መሆን የሚገባቸውን ሆነው ሳይገኙ ሲያይ በራሱም ሆነ በሌሎች ላይ መልካም ሳያደርጉ ሲመለከት ዘወትር እነርሱን ከመጥፎ ባህርያቸው ለመመለስ የሚተጋና በክፉ ፋንታ ክፉን የማይመልስ ሰው በመሆን ነው።

አገልጋይ የሚያገለግላቸው ሰዎች በእርሱ ላይ ክፉ ሲያስቡና ሲያደርጉበት አይቶ ያለምንም የፊት መጨማደድ እነርሱን ማገልገል ከቻለ ፍቅሩ አምላካዊ ፍቅር (አጋፔ) መሆኑን በተግባር ያሳያል። ይህ አገልጋይ ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ በተግባር ለእነርሱ በማሳየቱ የሚያገለግላቸው ሰዎች እንዴት እርስ በርሳቸውና ከሌሎች ሰዎች ጋር በፍቅር መኖር እንዳለባቸው ያስተምራቸዋል።

ሰዎች አገልጋይ እንደሚወዳቸው ሲረዱ የእርሱን መሪነትና ትምህርት ለመቀበል ያላቸው ፍላጎት ይጨምራል። አንድ ጌታን ለብዙ ዓመታት ያገለገለ አገልጋይ እኔ ገና ለወንጌል አገልግሎት ራሴን ስሰጥ "ሰዎችን ውደዳቸው፤ እነርሱም ይወዱሃል። ከተወደድክ ደግሞ አገልግሎትህን ይቀበላሉ። ነገር ግን ፍቅርን መጠበቅ ትተህ ከልባቸው እንዳያወጡህ ተጠንቀቅ" ብሎ መከረኝ። የዚህ አገልጋይ ምክር በጣም መሠረታዊ ነው። አገልጋይ ሰዎችን ከወደደና ተገልጋዮችም ተገቢውን ምላሽ ከሰጡት አገልግሎቱ የተቃና ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ግን

አገልጋዮች በፍቅር ይጀምሩና በጥል ይጨርሳሉ። አገልጋይ እንደ መጀመሪያው ተገልጋዮችን መውደዱን ያቆምና ምዕመኑን ለራሱ ዓላማ ማስፈጸሚያ ለመጠቀም መጠምዘዝ ይጀምራል። ይህን ጊዜ ምዕመናን አገልጋዮን ከልባቸው ውስጥ ያወጡታል። ከዚህ በኋላ ወደልባቸው ተመልሶ ለመግባት በሩ ይዘጋል። ይህ እንዳይሆን አገልጋይ ሁሉጊዜ የሚያገለግላቸውን ሰዎች መውደድ ይገባዋል። ፍቅሩም ከእውነተኛ ልብ የመነጨ እንጂ የሽንገላ መሆን የለበትም። እንዲህ ከሆነ የአገልጋዩ የፍቅር ሕይወት የጌታን ፍቅር ለሰዎች ያሳያል።

በፍቅር ምሳሌ መሆን ማለት ምዕመናን ሲሳሳቱ እውነትን አለመናገር ወይም አለመገሰጽ ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ፍቅር በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተና ኃጢአተኞችን የሚወድ ቢሆንም ከኃጢአት ጋር የሚተባበር አይደለም። አገልጋይ ለሚያገለግላቸው ሰዎች ያለው ፍቅር ኃጢአትን አይሸፍንም። ነገር ግን ኃጢአተኞች ንስሐ ገብተው ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ይጋብዛቸዋል።

አገልጋይ በታማኝነትም ምሳሌ ሊሆን ይገባዋል። አገልጋይ ለተናገራቸው ቃሎች ታማኝ መሆን አለበት። ለሰዎች የተናገረውን ቃል ያለበቂ ምክንያት ማጠፍ የለበትም። "አደርጋለሁ" ካለ ማድረግ አለበት። ቀጠሮን በሚገባ ማክበር ይጠበቅበታል። ይህ ቀላል ነገር ቢመስልም በተከታታይነት ቃሉን የሚያከብር ከሆነ ሰዎች ለሚናገራቸው ነገሮች ሥፍራ ይሰጣሉ፤ ያምኑታልም።

አገልጋይ በአደባባይ ለሚናገራቸው ቃሎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል። በመድረክ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሰው የለም በማለት የማይገባውን መናገር መልካም አይደለም። እንዲሁም ታማኝነቱን ፈተና ውስጥ የሚያስገባ ንግግር ከመናገር መቆጠብ አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች የአገልጋይን ታማኝነት የሚፈትኑት ትልቅ በሆኑ ነገሮች ሳይሆን በጣም ጥንቃቄን ሆነው ትኩረት በማይሰጥባቸው ነገሮች ነው።

አገልጋይ ለእግዚአብሔርም ታማኝ መሆን አለበት። ለእግዚአብሔር ምንም ዓይነት ዋጋ የሚያስከፍለው ነገር ቢመጣ የማይታጠፍ ታማኝነት ያለው ሰው መሆን አለበት። ሁኔታዎች መልካም ሲሆን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ቀላል ነው። ነገር ግን ሁኔታዎች አልመች ሲሉ፣ ኑሮ ሳይሳካ ሲቀር፣ መሠረታዊ ፍላጎት ለማማላት ምንም ነገር ሳይኖርም ታማኝ መሆን የእውነተኛ ታማኝነት መግለጫ ነው።

አገልጋይ ለቤተክርስቲያን ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል። አገልጋይ በጥሪው መሠረት ላስማራችው ቤተክርስቲያን ታማኝ መሆኑ አስፈላጊ ነው። ቤተክርስቲያን የእኔ አገልጋይ ነው ብላ ያስማራችው አገልጋይ ቤተክርስቲያንን በሚጎዳ በማንኛውም ተግባር ላይ ተሰማርቶ መገኘት የለበትም። አገልጋይ በቤተክርስቲያን መሠረተ እምነትና ደንብ መሠረት ለማገልገል ቃል እንደገባ ሁሉ በማንኛውም ሁኔታ ቃልኪዳኑን ማክበር ይኖርበታል። እንዲህ አለማድረግ በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት የገባውን ቃልኪዳን ማፍረስ ስለሆነ ታማኝነትን ማጉደል ነው። አገልጋይ በተጠራበት ቤተክርስቲያን ማገልገል የማይፈልግ ከሆነ ከቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ጋር በመነጋገር አገልግሎቱን አስረክቦ

ወደሚፈልግበት ሥፍራ መሄድ ይችላል። ውሳኔው የግሉ ሲሆን ታማኝነት በማጉደል ግን አይከሰስም።

አገልጋይ ምሳሌ በመሆን ሲኖር ለራሱና ለተከታዮቹ መልካም ውጤት አለው። አገልጋይ በምሳሌነቱ የራሱን ትክክለኛ ማንነት በግልጽ ማሳየት ይችላል። በዚህ ጊዜ ምዕመናን እግዚአብሔር መልካም አገልጋይ እንደሰጣቸው ይረዳሉ፤ እርሱን በመመልከትም እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ያድጋሉ።

ምሳሌ መሆን በቤተክርስቲያን አገልጋዮች ተቀባይነት ሲያገኙ ወይም ሁኔታዎች ሁሉ በተመቻቹበት ወቅት ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮችን የሚቃወሙ ወገኖች ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች የአገልጋዮችን አገልግሎት ከመደገፍ ይልቅ መሰናክል ይሆናሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔር ሰው በመሆን ምሳሌነትን ማሳየት እጅግ አስፈላጊ ነው።

*ገሠሠ ለአገልግሎት ሲወጣ የሃያ ሦስት ዓመት ሊጋ ጎልማሳ ነበር። እርሱ ለማገልገል በተመደበበት አካባቢ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ደግሞ ዕድሜያቸው ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ ከመሆናቸውም በላይ በአገልግሎት ውስጥ ለብዙ ዓመታት የቆዩ ነበሩ። ገሠሠ ከእነርሱ ይልቅ መደበኛ ትምህርት የተማረ በመሆኑ አገልግሎቱ መስመር የያዘ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተምር በሚገባ ተዘጋጅቶበት ፈር ባለው ሁኔታ ያስተምራል። ከዚህም የተነሳ ምዕመናን እየወደዱት መጡ። የቤተክርስቲያን መሪዎችም መደበኛ ትምህርት የተማረና ጌታ የሚጠቀምበት አገልጋይ ስለሆነ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን እንዲያስተባብር ኃላፊነት ሰጡት። በዚህ ጊዜ ከእርሱ በፊት የነበሩ አገልጋዮች ቀኑበት። የገሠሠን ስም ለማጥፋት መልካም ያልሆኑ ነገሮችን ያስወሩበት ጀመር። ለዋናው የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢም የገሠሠ ሕይወትና አገልግሎት መልካም እንዳልሆነ ሪፖርት አደረጉ። መጋቢው ሁኔታውን ሲከታተል የተወራው ነገር ትክክል አለመሆኑ ተገንዝቦ ዝም አለ። ከጥቂት ወራት በኋላ ገሠሠም የተወራበትን ነገር ሰማ። በጊዜው በነበረው የማስተባበር ሥልጣን ተጠቅሞ ያስወራበትን አገልጋይ መጉዳት ቢችልም ይህ መንገድ ጥሩ አለመሆኑን በመገንዘብ በፊት ያሳየው ከነበረው ፍቅር የበለጠ ፍቅር ማሳየት ጀመረ። በዚህም የአገልጋዩ ልብ ተነካ፤ ስላደረገውም ነገር ይቅርታ ጠየቀ። ገሠሠ አሁን በአካባቢው ምዕመናንና አገልጋዮች ዘንድ የተወደደ አገልጋይ ነው።*

የመምራት ሥልጣን የተሰጣቸው አገልጋዮች ከሚያገለግሏቸው ምዕመን ወይም ከሚመሯቸው አገልጋዮች መካከል የሚቃናቀናቸው ሰው ሲያገኙ በሁለት መንገድ ሁኔታውን ማስተናገድ ይችላሉ። የመጀመሪያው ባላቸው ሥልጣን ተጠቅመው ተቀናቃኙን ማንበርከክ ነው። በዚህ መንገድ ሰዎቹን ማሸነፍ የሚቻለው ለጊዜው ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔር አሳብ ያለበት መንገድ አይደለም። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ መልካም ምሳሌነትን እያሳዩ ማለትም የክርስቶስን ፍቅር እያሳዩ በመልካም ተግባር ማሸነፍ ነው። በዚህ መንገድ ሰዎቹን በዘላቂነት ማሸነፍ ይችላሉ። ይህ የእግዚአብሔር አሳብ ነው።

3. **ከተለያዩ ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መኖር** (1ጢሞ 5፡1-2፤ 2ጢሞ.2፡22)

በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ። በዕድሜያቸው ያረጁ ወንዶችና ሴቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶች፣ ልጆች፣ እንዲሁም ከኑሮ ደረጃ ደግሞ ሐብታሞችና ድሆች፣ ከትምህርት አኳያ ደግሞ መደበኛ ትምህርት ያላቸውና የሌላቸው፣ ከአገልግሎት አኳያ ደግሞ በአገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉና የማይሳተፉ ለምሳሌ ሽማግሌዎች እና ተራው ምዕመናን እንዲሁም በተለያዩ መስፈርቶች የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ማግኘት ይቻላል። አገልጋዮች ከእነዚህ የተለያዩ ሰዎች ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።

በሀገራችን ባህል ሽበት ክብር አለው። የእግዚአብሔር ቃልም ሽበት ክብር እንደሆነ ይናገራል (ምሳ.16፡31፤20፡29)። ስለዚህ በዕድሜ ያረጁ አባቶችና እናቶች ክብር ሊያገኙ ይገባቸዋል። ምክንያቱም ረጅም ዕድሜን የሚሰጠው እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። ስለሆነም አገልጋዮች በዕድሜ ትላልቅ የሆኑ ሰዎችን እንደ አባትና እንደ እናት ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

አገልጋዮች ወጣት ከሆኑ ሰዎች ጋር ደግሞ ንጽሕና ያለው ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። ብዙ ጊዜ የቅድስና ጉድለት የሚመጣው አገልጋዮች ወጣት ከሆኑ ሰዎች ጋር በሚኖራቸው ቅድስና የሌለበት ግንኙነት ነው። ስለዚህ አገልጋዮች ወጣቶችን እንደ ወንድሞችና እህቶች በመቁጠር ተገቢና ወሰኑን የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ አለባቸው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸውም ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ማድረግም ይገባቸዋል። በተለያዩ ምክንያቶች የኑሮ ወይም የተለያየ ችግሮች ያለባቸው ምዕመናን መረሳት የለባቸውም። አገልጋዮች ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖር በማድረግ ምዕመናን እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና በዚህ ሁኔታ ለመርዳት ከአቅም በላይ የሆኑባቸውን ሰዎች ደግሞ ቤተክርስቲያን እንድትረዳቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ሐብታም የሆኑትን ሰዎች ደግሞ ከሌሎች ይልቅ ሥፍራ መስጠትና የተለየ ክብር መስጠት አይገባም። ባለጠግነት መልካም ነው፤ ሆኖም ባለጠጎች ከእግዚአብሔር ይልቅ በሀብታቸው እንዳይታመኑ ማስተማር አስፈላጊ ነው። አገልጋዮች ሀብታሞች ካላቸው ሀብት ለሌሎች እንዲሁም ለቤተክርስቲያን መስጠትን እንዲለማመዱ መምከር አለባቸው (1ጢሞ.6፡17-19)። አገልጋዮች የባለጠጎችን ሀብት ለራሳቸው ለማግኘት ብለው ከእነርሱ ጋር ጽድቅ የሌለበት ግንኙነት ማድረግ ከቶ አይገባቸውም። በዚህ ዘመን ብዙ አገልጋዮች ሀብት ያላቸውን አማኝ ነጋዴዎችን በተለይ ብዙ ትምህርት የሌላቸውን እንደሚሹ ይስተዋላል። ይህም በእግዚአብሔር ስም እየሄዱ ለራሳቸው ምጽዋት ለመሰብሰብ ነው። አገልጋዮች ራሳቸውን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማስገባታቸው አገልግሎታቸውንና ራሳቸውን ማዋረዳቸው እንደሆነ መገመት አያዳግትም።

አገልጋዮች በቤተክርስቲያን ከሚያገለግሉ ሌሎች አገልጋዮች እና የቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ተገቢ የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባቸዋል። አገልጋዮችን እንደ አብረው ሠራተኞች(የሥራ ባልደረባ) ማየትና የእነርሱንም ጸጋና አገልግሎት መባረክ እንዲሁም መደገፍ አስፈላጊ ነው። ሌሎች አገልጋዮችን "ለምን ከእኔ ተሻሉ?" በሚል ሰንፈስ የእነርሱን ማንነት መንካት፣ አገልግሎታቸውን መተቸትና ማንቋሸሽ የራስን ትክክለኛ ማንነት (የእግዚአብሔር አገልጋዮች አለመሆናቸውን) ለሰዎች ማጋለጥ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። አገልጋዮች ስለሌሎች አገልጋዮች መጥፎነት ሲያወሩ ራሳቸው መጥፎዎች እንደሆኑ መስበካቸው እንደሆነ ሊያስተውሉ ይገባቸዋል። እነርሱም ስለሌሎች በሚናገሩት ነገር ይመዘናሉ። ስለዚህ አገልጋዮች እርስ በርስ መደጋገፍ እንጂ እርስ በርስ መነቃቀፍና ለሹመት ትግል ማድረግ አይጠበቅባቸውም።

በአንዳንድ ቤተክርስቲያናት አንድ ላይ የሚያገለግሉ አገልጋዮች እርስ በርሳቸው አብረው መጸለይና መደጋገፍ ቀርቶ ሰላምታም ሰው ሲኖር ብቻ የሚጠየቁ አሉ። የቤተክርስቲያን ምዕመናን እንኳ ስምተው ለማስታረቅ ሲሞክሩ ለመታረቅ እምቢ ብለው ግን በዚያው ቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ አገልጋዮች መኖራቸው ያሳዝናል። ለእነዚህ አገልጋዮች የአገልግሎት ምንነት ቀርቶ የክርስትና እምነት ትርጉምም የገባቸው አይመስለኝም። ሌላው ቀርቶ "የምናገለግላቸው ሰዎች ምን ይሉናል?" በማለት እንኳ በመካከላቸው ያለውን ችግር መፍታት ነበረባቸው። አገልጋዮች እርስ በርሳቸው መልካም ግንኙነት ሳይኖራቸው እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ መልካም ሥራውን እንደልቡ ያደርጋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። የእግዚአብሔር ኃይል በሙላት እንዲሠራ መስማማትና አብሮ የእርሱን ፊት መፈለግ አስፈላጊ ነው። አገልጋዮች እርስ በርሳቸው በመልካም ግንኙነት በመኖር ለሚያገለግሉት ምዕመናን ተስማምተው መኖርን በምሳሌነት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት በአገልጋዮች መካከል የግንኙነት ችግር እየፈጠረ ያለው ነገር መጋቢ ሆኖ ለመሾም ሁሉም እሽቅድምድም ማድረጉ ነው። አገልጋዮችን በተጠሩበት የአገልግሎት መስክ ከማሰማራትና ሁሉም የአገልግሎት ስጦታዎች እኩል እንደሆኑ ከማሰብ ይልቅ የቤተክርስቲያን የመጋቢነት አገልግሎትን እንደ ትልቅ የአገልግሎት ደረጃ መመልከት የችግሩ መንስኤ ነው። በእንድ በኩል ቤተክርስቲያን አገልጋዮችን መጋቢ የምታደርገው አገልግሎቱን በማየት ለመልካም አገልግሎቱ እውቅና ለመስጠት ወይም እንደ ደረጃ ዕድገት ስለሆነ ሁሉም ይህችን ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ይህም ቢሆን እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ቦታ ሆኖ በታማኝነት እግዚአብሔርን በማገልገል የአገልግሎት የደረጃ ዕድገት ላገኙትም አገልጋዮች እግዚአብሔርን ማመስገን እጅግ የከበረ ነገር ነው።

ከቤተክርስቲያናቸው ውጭም ቢሆን አገልጋዮች በንጹህ ልብ እግዚአብሔርን ከሚያመልኩና በጽድቅ ከሚኖሩ አገልጋዮችና ምዕመናን ጋር ፍቅርና ሰላም ያለበትን ጤናማ ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ። ከማንኛውም ቤተእምነት ቢሆኑ ጌታን በሕይወታቸው ከሚከተሉ

እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ጋር መልካም ግንኙነት ማድረግ ይቻላል። ይህ አሳብ እንዲህ ዓይነት ሕይወት ከሌላቸው ሰዎች ጋር ደግሞ የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ እንደሚገባቸው አይገፋፋም።

አንዳንድ አገልጋዮች ራሳቸውን ከሰው በላይ ልዩ እንደሆኑ ስለሚቆጥሩ ምዕመናን ወደ እነርሱ ቀርበው በየጊዜው የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ማወያየት አይችሉም። ምዕመናኑ ወደ እነርሱ መቅረብ አይፈልጉም፤ አገልጋዮቹም እንዲህ ያሉትን ምዕመናን አይቀርቡም። የምዕመንን ችግር አውቀው በሚገባ ለማገልገል አገልጋዮች ራሳቸውን ከሚያገለግሉአቸው ምዕመናን ጋር ማመሳሰል ይኖርባቸዋል። ምዕመናን "የእኛ ሰው ነው" ወይም "እኛን ይመስላል" ማለት አለባቸው። እንዲህ ከሆነ ከምዕመናን ጋር መልካም ግንኙነት ኖሮአቸው በተገቢው መንገድ ማገልገል ይችላሉ።

4. **ለራስ ጤንነት መጠንቀቅ** (1ጢሞ.5:23)

ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ስለሆነ አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ተገቢ ነው። ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው (1ቆሮ.6:19)። ስለሆነም ሰውነትን ከሚጎዳ ከማንኛውም መጥፎ ባህርይ መጠበቅ ይገባል። ይህ ሰውነትን ሊጎዳ ከሚችል ነገር ለምሳሌ ከክፉ አሳብና ምኞት እንዲሁም ድርጊት መራቅን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ከአጉል ልማድ ውጭም በሽታ ሲይዝ አስፈላጊውን የሕክምና እንክብካቤ ማግኘትን ያመለክታል። አገልጋዮች ሰውነታቸው ሲታመም እግዚአብሔርን እንደሚገባ ማገልገል ይሳናቸዋል። ስለዚህ ተመጣጣኝ ምግብ በመመገብ እንዲሁም መድኃኒት በመውሰድ ራሳቸውን ከበሽታ መከላከል አለባቸው።

5. **ከገንዘብ ፍቅር መሸሽ** (1ጢሞ.6:11)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ገንዘብ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ እንደ አምላክ ተቆጥሮ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚፎካከር ጠቅሷል (ማቴ.6:24)። ክርስቲያን ወይም አማኝ መሆን የገንዘብ ማግኛ መንገድ አይደለም። እግዚአብሔርን መምሰል ገንዘብ የማትረፊያ መስመር አይደለም። ሰዎች አማኝ ወይም አገልጋይ የሚሆኑት በዚያ ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት ከሆነ የልብ መሻታቸው ከትክክለኛ የእግዚአብሔር አሳብ ለይቶአቸዋል። የእነርሱ እምነትም ሆነ አገልግሎት ከንቱና ስህተት ነው። አገልግሎትን ወይም እምነታቸውን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ሀብት ማከማቸት እንደሆነና እግዚአብሔርን መከተል ወይም ማገልገል ሀብታም ያደርጋል ማለት የጌታ ኢየሱስ እውነተኛ ወንጌል አይደለም። አማኞች (ምናልባትም ጥቂት አገልጋዮች) ሀብታም ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን የእነርሱ ሀብታም መሆን የእነርሱን የጽድቅ ሕይወት ወይም የአገልግሎት ታላቅነት አያመለክትም።

አገልጋዮች እግዚአብሔር በሰጣቸው ጥቂት ነገር ደስ እያላቸው ከገንዘብ ስግብግብነት ራሳቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል። ለአገልጋዮች

ገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር አስፈላጊ ሲሆን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን እየለመኑ ባላቸው ነገር እግዚአብሔርን እየመሰገኑ መኖርን መለማመድ ትልቅ ጸጋ ነው። የአገልጋዮች ልብ በገንዘብ ፍቅር ከተነደፈ ትኩረታቸው ከአገልግሎት ይልቅ ገንዘብን በማሳደድ ላይ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች ሳያውቁ በገንዘብ ፍቅር ይነደፋሉ። አንዳንድ አገልጋዮች ሁልጊዜ እየተጋበዙ በተለያዩ ቦታዎች ያገለግላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት በአገልግሎቱ የሚያገኙትን የትራንስፖርት ወይም የአገልግሎት ስጦታ ለመሰብሰብ ነው። በዚያ በሚያገኙት ነገር የቤታቸውን አንዳንድ ቀዳዳዎች ለመሸፈን ያስባሉ። ከጊዜ በኋላ አገልግሎቱ ይረሳና ገንዘቡ ስፍራውን ይይዛል። ከዚያም ደሃ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ሀብት አላቸው ወደሚባሉ ቤተክርስቲያናት ሄደው ማገልገልን ይመርጣሉ። ይህን አሳብ ያነሳነው ከአገልግሎት በኋላ ለትራንስፖርት ተብሎ የሚሰጠውን ገንዘብ መቀበልም ሆነ አለመቀበል ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመናገር ሳይሆን ከገንዘብ ጋር የተያያዘውን የአንዳንድ አገልጋዮችን አገልጋዮችን የልብ ሁኔታ በማሳየት እያንዳንዳችን ከገንዘብ ፍቅር እንድንጠነቀቅ ለማስገንዘብ ነው።

*ጥላሁን ለአገልግሎት ወደተለያዩ ቦታዎች ሄዶ ሲያገለግል የትራንስፖርት ገንዘብ ተብሎ ሲሰጠው የቤተክርስቲያን መባ ውስጥ ጨምሩልኝ ይላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በተለይ አገልግሎቱ ከቤቱ እሩቅ ቦታ ከሆነ ይወስዳል፣ ቅርብ ቦታም ሆኖ የሚወስድበት ሁኔታ አለ። አንዳንድ ጊዜ ዛሬስ ስንት ብር ይሰጡኝ ይሆን? የሚል አሳብ በውስጡ ሲሰማው የትራንስፖርቱን ገንዘብ አይቀበልም። ልቡ ግን ስለገንዘብ የማያስብ ከሆነ ይቀበላል።* በዚህ ሁኔታ አገልጋዮች ልባቸውን ስለሚያውቁ አሳባቸውን መፈተሽና ተገቢ የሆነውን ነገር ማድረግ ይችላሉ።

ገንዘብ በራሱ መልካም ወይም ክፉ አይደለም። ክፉ የሚያደርገው አገልጋይ ለገንዘብ ያለው አመለካከትና አያያዝ ነው። ገንዘብ ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል። ወንጌልን ያለገንዘብ ማገልገል አይቻልም። ለጌታ ኢየሱስም አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ወገኖች ነበሩ (ሉቃ8:3)።

ነገር ግን ገንዘብ ቅድሚያ ከተሰጠውና ፍቅሩ ካየለ ክፉ ይሆናል። የገንዘብ ፍቅር የማይጠገብ ረሃብና የማይረካ ጥም ነው። አንድ ሰው በገንዘብ ፍቅር ከተያዘ ብዙ ገንዘብ ቢያከማችም "በቃኝ" የሚልበት ደረጃ ላይ አይደርስም። የገንዘብ ፍቅር ጨዋማ ውኃ እንደመጠጣት እንደሆነ ይነገራል። ጨዋማ ውኃ በምንም መልኩ የጠጪውን ጥም ሊያረካ አይችልም። እንዲያ መጠጣት ከጀመረ አሁንም አሁንም እንዲጠጣ ይገፋፋዋል። ምክንያቱም ጥሙን ማርካት አይችልም። ይህ ሰው መርካት የሚችለው ጨው የሌለበትን ውኃ ከጠጣ ብቻ ነው። ስለዚህ የገንዘብ ፍቅር እርካታ የለውም።

6. **ከክፉ ምኞት መሸሽ** (2ጢሞ.2:21)

እግዚአብሔር ያልነጹትን ሰዎች ማንጻት ቢችልም ለአገልግሎቱ የሚጠቀምባቸው አገልጋዮች ግን ከክፉ ምኞት የራቁ እንዲሆኑ

ይፈልጋል። ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቁ የሚሆኑ ሰዎች ራሳቸውን በቅድስና የሚጠብቁ ናቸው። በተለይ ወጣት የሆኑ አገልጋዮች ወጣትን ከሚፈታተኑ ክፉ የወጣትነት ምኞቶች መሸሽ ይጠበቅባቸዋል። የወጣትነት ጊዜ ክፉ ምኞቶች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹ የወሲብ ምኞት፣ ያለመታዘዝ መንፈስ፣ በራስ የስኬት ምኞት መጋለብ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆን እና የመሳሰሉት ናቸው። አገልጋይ ከእነዚህና እነዚህን ከሚመስሉ ነገሮች መሸሽ አለበት። መሸሽ የሚለው አሳብ ከኋላ ለመጉዳት ከሚያሳድድ ነገር ለማምለጥ ወደፊት መሮጥ ማለት ነው። ለመጉዳት ለሚያሳድድ ነገር ጀርባን መስጠት ነው።

እንግዲህ ሰዎች አካልን ሊጎዳ ከሚችል ጠላት ለማምለጥ እንደሚሮጡ ሁሉ እንዲሁ አገልጋይም ነፍስንና መንፈስን ከሚጎዳ ከማንኛውም ጎጂ ነገር መሸሽ አለበት። ኃጢአትን ለማሸነፍ ዓይነተኛው መንገድ መሸሽ ነው። ከኃጢአት ጋር በመደራደር ማሸነፍ አይቻልም። አገልጋይ እንደ ዮሴፍ ጀርባውን ለኃጢአት በመስጠት መሸሽ ይገባዋል። የእግዚአብሔር ቃል አገልጋዮች (ምዕመናንም ጭምር) ከዝሙት (1ቆሮ.6:18)፣ ከጣዖት አምልኮ (1ቆሮ.10:14) እና ከገንዘብ ፍቅር (1ጢሞ.6:11) እንዲሸሹ ያስጠነቅቃል።

አገልጋይ ከላይ ከተጠቀሱ ነገሮች በሚሸሽበት ጊዜ ከአንድ ጎጂ ነገር ወደሚጠቅም ነገር ይሮጣል። ከአንዱ ለማምለጥ ሌላውን ደግሞ ለመያዝ ነው- ሩጫው። አገልጋይ ሊከተላቸው የሚገባው መልካም ነገሮች ደግሞ አሉ። መከተል የመሸሽ ተቃራኒ ነው። መሸሽ ላለመያዝ ሲሆን መከተል ደግሞ ለመጨበጥ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ከኃጢአት በመሸሽ የጽድቅን ሕይወት ለመያዝ ዕለት ዕለት ወደፊት ይሮጣል። ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት የተዋጣለት አገልጋይ መልካም ያልሆነውን ነገር በመተው የእግዚአብሔርን አሳብ ለማወቅና ለማድረግ ወደፊት የሚገሰግስ ነው። አሮጌውን ነገር ጥሎ በክርስቶስ ያለውን አዲስና የተቀደሰ አሳብ ለመያዝ መዘርጋት ለአገልግሎት ወሳኝ ነው። በአንዳንድ ሁኔታ ውስጥ ሲታይ በዘመናችን አንዳንድ አገልጋዮች መሸሽ ወደሚገባቸው ነገር ይሮጣሉ፤ የተጠሩበትን ዓላማ ሊያደናቅፍ ለሚችል ነገር ራሳቸውን እየሰጡ ይገኛሉ።

## 7. በተረዳበትና በተማረበት ጸንቶ መኖር (2ጢሞ.3:14)

አገልጋይ ወደ አገልግሎት ከመምጣቱ በፊትና በኋላ ከታመኑ የእምነት አባቶች የተማረውን ትክክለኛ የእምነት ትምህርት በጽናት መያዝና በዚያም ትምህርት መኖር አለበት። አገልጋይ ከእግዚአብሔር ቃልና ከቤተክርስቲያን አባቶች የተረዳውን መልካሙን ትምህርት እንዲሁም በሕይወታቸው ያየውን መልካም ምሳሌነት መከተል አለበት። አገልጋይ በዘመናዊነት መንፈስ ተሞልቶ በፊት የተማረውን እውነት መጣል የለበትም። እውነትና መልካም ሕይወት ሁልጊዜ አይለወጡም።

አገልጋይ እውነት ከሚመስል ግን ሐሰት ከሆነ ትምህርት በመራቅ ከታመኑ ምንጮች ያገኘውን እውነት አጥብቆ በመያዝ ከኖረበት የተጠራበትን ተልዕኮ ከግብ ማድረስ ይችላል። በአሁኑ ጊዜ አንድ

አገልጋይ በመንፈሳዊ አመለካከቱ ዘመናዊውን የማይቀበል ከሆነ እንደ ኃላ ቀር ይቆጠራል። በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፈውን መንፈሳዊ ትምህርትና ልምምድ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነውን ነገር እንዲቀበል ግፊቱ ኃይለኛ ነው። የመንፈሳዊ ዕውቀትና ልምምድ ማደግ መልካም ነው። ግን አዲስ ትምህርትና ልምምድ ቀድሞ የተማርነውንና የተረዳነውን እውነት የሚያፈርስ ከሆነ ልናስተናግደው አይገባንም። ዘመናዊ የሆኑትን መንፈሳዊ ትምህርቶችንና ልምምዶችን እየተከተልን ምዕመናቻችን እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ ማስተማርም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ እውነትን ለሰዎች በማስተማር እውነት ያልሆነውን ነገር እንዲያውቁ ማድረግ ነው። ምክንያቱም ሰዎችን አርነት የሚያወጣው እውነትን መረዳት ነው እንጂ ስህተት የሆነውን ነገር ማወቅ አይደለም (ዮሐ.8:32)።

8. **በጊዜውም አለጊዜውም ጸንቶ ማገልገል** (2ጢሞ.4:2፣5)

በጥሪ ለወንጌል አገልግሎት መውጣት መስዋዕትነት ያስከፍላል። አገልጋይ ሁኔታዎች ምቹ ቢሆኑም ባይሆኑም አገልግሎቱን መቀጠል ይጠበቅበታል። ሁኔታዎች በተመቻቹበት ጊዜ (ለምሳሌ ከውስጥና ከውጭ ፈተናና ስደት በሌለበት ጊዜ) አገልጋይ በተገኘው መልካም አጋጣሚ በመዘናጋት አገልግሎቱን ችላ ማለት እንደሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ያሳስባል። ምቹ ጊዜ ለወንጌል አገልግሎት ጥሩ እንደሆነ ሁሉ እንቅፋትም ሊሆን ይችላል። አገልጋይ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ትኩረቱ ከወንጌል አገልግሎት የዓለምና የግል ሥጋዊ ነገሮችን ወደ ማሳደድ በመመለስ ለወንጌል አገልግሎት የነበረው ቅንዓት ሊቀንስ ይችላል።

አለጊዜውም የሚለው አሳብ ደግሞ ሁኔታዎች ለወንጌል አገልግሎት የማይመቹበት የመከራና የስደት ጊዜ ነው። በዚህ ሁኔታ የወንጌል አገልጋይ መሆን ዋጋ ያስከፍላል። አገልጋይ በሕይወቱ በመወራረድ ማገልገል የግድ ይሆንበታል። አንዳንድ አገልጋዮች ስደት ሲመጣ አገልግሎታቸውን ትተው እንደምዕመን ብቻ ለመኖር ይወስናሉ። አንዳንዶች ደግሞ ስደቱን በመፍራት ጌታን ትተው ወደ ዓለም ይገባሉ። መከራና ስደት ሲመጣ አንድ ቀን የሚያልፍና መልካም ዘመን እንደሚመጣ አይታሰባቸውም። በስደትና በመከራ ውስጥ ሆኖ "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው፤ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት የሚያሳልፈኝን ጸጋ ይሰጠኛል፤ ብሞትም ብኖርም ለጌታ ነው" ብሎ መወሰን እና ማመን ቀላል አይደለም። ጥቂቶች ግን እንዲህ ዓይነት ቆራጥ ውሳኔ በማድረግ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው ጌታን ያገለግላሉ። እውነትም የጌታን ሥራ ለመሥራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ለሰጡ አገልጋዮች ጸጋው ይበዛላቸዋል።

መከራና ስደት አንዳንድ አገልጋዮችን ከአገልግሎት ቢመልሳቸውም አንዳንዶችን ግን የበለጠ በማጥራት በአገልግሎት እንዲጸኑ አድርጓቸዋል። ከመከራና ስደት ይልቅ አገልጋዮችን ለዘብተኛ የሚያደርጋቸው ምቾት ነው። አንዳንድ የዘመኑ አገልጋዮች ልባቸው የተሰለበ ወታደሮች ናቸው። በመድረክ ላይ ከመሬጥ ያለፈ ለወንጌል መስዋዕትነት ለመክፈል

ፈቃደኞች አይደሉም። ምቹ ጊዜ ሲመጣ የአገልጋዮች አጀንዳ ከወንጌል ወደ ድርጅታዊ፣የቡድን ወይም ግላዊ አጀንዳዎች ይለወጣል። አገልጋዮች እንዴት ወንጌል ይስፋፋል? ምዕመናን እንዴት የተሻለ መንፈሳዊ አገልግሎት ያገኛሉ? የሚሉትን ነገሮች ተወት በማድረግ እንዴት ትምህርት ቤት ገብቼ ራሴን ላሻሽል? እንዴት ባደርግ የደመወዝ ጭማሪ ማግኘት እችላለሁ? የቤተክርስቲያን መሪ እንዴት ልሁን? የሚሉ አጀንዳዎች ትኩረት እያገኙ ይመጣሉ። እነዚህ አጀንዳዎች በራሳቸው ክፉዎች ባይሆኑም የወንጌልን አጀንዳ ወደኋላ የሚያስቀሩ ከሆኑ ግን ወንጌልን ለማራመድ መሣሪያዎች ከመሆን ይልቅ ወንጌል እንዳይስፋፋ እንቅፋት ይሆናሉ።

ስለዚህ አገልጋይ ምንጊዜም(ማለትም ሁኔታዎች ሲመቹም ሆነ ሳይመቹ) ትኩረቱ በተጠራበት የወንጌል አገልግሎት ላይ መሆን ይኖርበታል። እንዲህም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ በሚያገለግልበት ወቅት የተለያዩ ተግዳሮቶች ያጋጥሙታል። እነዚህ ተግዳሮቶችና መንስኤዎቻቸው ምን እንደሆኑ፣ እንዴትስ ማሸነፍ እንደሚቻል ማወቁ ጠቃሚ ነው።

እንግዲህ ለአገልግሎት ስኬት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ለአገልጋዩ የሚሰጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ሳይሆን አገልጋዩ ያለው ባህርያትና የሕይወት ዘይቤውም ጭምር ነው። አገልጋይ የሚኖረው የሕይወት ዘይቤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ከሆነና በኑሮውም ሆነ ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት «ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር ምን ይላል?» በሚል መርሕ አሳብ ከሆነ ራሱን እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ማቅረብ ይችላል። የአገልጋይ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ዓላማና ግንኙነት የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከላዊ ያደረገ መሆን አለበት። እንዲህ ሲሆን ራሱንና ሌሎችን ሊጠቅም በሚችል ጎዳና ይሄዳል። እነዚህ መልካም ባሕርያት በአንድ ጊዜ ከሕይወት ጋር ተዋሕደው የማይጠፉ ነገሮች ባለመሆናቸው ዘወትር እንክብካቤ ሊሰጣቸውና በጥንቃቄ ተከትትለው ሊያድጉና ሊጠበቁ ይገባቸዋል።

---

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን መስሎ መኖርን እንዴት ትረዳዋለህ?
2. በምታገለግልበት ቤተክርስቲያን ሰዎች በምን በምን ምሳሌ እንደሆንክላቸው ይመሰክራሉ?
3. ከመሪዎች፣ ከሌሎች አገልጋዮች እንዲሁም ከምዕመናን ጋር ያለህ ግንኙነት ምን ይመስላል? ለግንኙነትህ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ምንድናቸው? እንዴትስ ሊታስወግዳቸው ትችላለህ?
4. አገልጋይ ለገንዘብ ያለው ቅርበትና ርቀት (የገንዘብ ፍቅር መኖሩና አለመኖሩ) በምን ይለካል?
5. በአገልግሎትህ በጣም የምፈትንህ ነገር ምንድነው? እንዴትስ እየተከላከልክ ትገኛለህ?